# የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

# መክፈቻ

-- *Ex Libris* --
B. N. Lapsley
375 Willow Wood
Murphy, Texas 75094

የቃለ ሕይወት ሥነ ጽሑፍ ድርጅት
የፖስታ ሣጥን ቁጥር 127
አዲስ አበባ ።

# ማሳሰቢያ

ይህንን «የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት መክፈቻ» ተብሎ የተዘጋጀውን መጽሐፍ አንብቦ የጨረሰ ሁሉ «የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት መክፈቻ» በመባል ከዚህ በፊት የታተመውን መጽሐፍ ማንበብ ይገባዋል ። እነዚህ ሁለቱ መጻሕፍት በጠቅላላው ስለ መጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት በመጠኑ እንዲያስረዱ የተዘጋጁ ስለ ሆነ ለካህን ፥ ለተማሪ ሆነ ለማናቸውም ሰው በጣም ጠቃሚ ናቸው ።

# ማውጫ


| | ገጽ |
|---|---|
| መግቢያ | 4 |
| ዘፍጥረት | 8 |
| ዘጸአት | 9 |
| ዘሌዋውያን | 10 |
| ዘኁልቍ | 11 |
| ዘዳግም | 11 |
| ኢያሱ ወልደ ነዌ | 12 |
| መሳፍንት | 13 |
| ሩት | 14 |
| ሳሙኤል ቀዳማዊ | 14 |
| ሳሙኤል ካልዕ | 15 |
| ነገሥት ቀዳማዊና ነገሥት ካልዕ | 16 |
| ፩ኛና ፪ኛ ዜና | 17 |
| ዕዝራ | 18 |
| ነህምያ | 19 |
| አስቴር | 19 |
| ኢዮብ | 20 |
| መዝሙረ ዳዊት | 21 |
| ምሳሌ | 21 |
| መክብብ | 22 |
| መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን | 23 |
| ነቢያት | 23 |
| ትንቢተ ኢዩኤል | 24 |
| ትንቢተ ዮናስ | 25 |
| ትንቢተ አሞጽ | 26 |
| ትንቢተ ሆሴዕ | 26 |
| ትንቢተ ኢሳይያስ | 27 |
| ትንቢተ ሚክያስ | 28 |
| ትንቢተ ናሆም | 29 |
| ትንቢተ ሶፎንያስ | 29 |
| ትንቢተ ኤርምያስ | 30 |
| ሰቆቃው ኤርምያስ | 31 |
| ትንቢተ ዕንባቆም | 32 |
| ትንቢተ ዳንኤል | 32 |
| ትንቢተ ሕዝቅኤል | 34 |
| ትንቢተ አብድዩ | 35 |
| ትንቢተ ሐጌ | 36 |
| ትንቢተ ዘካርያስ | 36 |
| ትንቢተ ሚልክያስ | 37 |
| በብሉይና በአዲስ ኪዳን መካከል ያሉት ዘመናት | 38 |
| መሢሑ | 39 |

# መግቢያ

በአሁኑ ዘመን ስለ ትምህርት የሚደረገው ጥረት ከመቼውም ይልቅ ተወዳ ዳሪ የሌለው ነው። መጻሕፍትንም መመራመር የብዙ ብልሆች ሰዎች መልካም የጊዜ ማሳለፊያ ሆኖአል። መጻሕፍት በብዛትና በአነስተኛ ዋጋ ማግኘት ይቻላል። እንግዲህ በዚህ በዛሬው ጊዜ ከመጻሕፍት ሁሉ የበላይነት ያለው መጽሐፍ ቅዱስን በዚህች በኢትዮጵያ ምድር ያሉ ታላላቆችና ታናናሾች የመጀመሪያ ምርጫቸው በማ ድረግ ሲገለገሉበት ከማየት የበለጠ ደስታ ምን አለ?

መጽሐፍ ቅዱስ ከ2000 ዓመታት በላይ በፈጀ ዘመን 40 በሚሆኑ ሰዎች በእ ግዚአብሔር መሪነት ተጻፈ። ከእነዚህም መጻሕፍት እንደ ወንጌላት፣ መዝሙረ ዳዊት፣ ዘፍጥረት ያሉትና ሌሎችም ብዙዎች ታወቁ። የቀሩት መጻሕፍት ግን ምንም እንኳ የእግዚአብሔር ቃል ክፍሎች ቢሆኑም ከጥቂት ሰዎች በቀር ያወቃ ቸው አልነበረም። ዓለም ራሷን ልታጠፋ በተቃረበችበት ጊዜ፤ ጊዜም ራሷ ዓለም በገዛ እጅዋ ለመጥፋት የምትዘጋጅ መሆንዋን በማውሳት በምትጮህበት ጊዜ፤ እግዚ አብሔር ለዚህ ዘመን ያለውን አቅድ ማወቅና በየመንገዳችንም ከማዘንበል መወሰን ለየአንዳንዳችን አስፈላጊና ተገቢ ነው።

የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ለብሉይ ኪዳን ጥናት በር መክፈት ነው። በእያንዳ ንዱ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙትን ዋና ዋና አሳቦች ለመከታተል እንዲመች በመተን ተን፤ በተጨማሪም በተለይ ህሊናን ማራኪ የሆኑትን ነገሮች ለመረዳት የሚረዱ ማስታወሻዎች በማድረግ 39ኙም መጻሕፍት ተዘርዝረዋል። መጽሐፉ በጠቅላላ የሚ ገልጸው በብሉይ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔር ሰዎች የነበሩትን አይሁዳውያን ታሪክ ቅደም ተከተል መሠረት በማድረግ ነው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት ዘመናት እንደ ኢትዮጵያ አቈጣጠር ነው። አብዛኛዎቹ የትንቢት መጻሕፍት የተጻፉት ፩ኛና ፪ኛ ነገሥት በተጻፈበት ዘመን ነው። በዚህ መጽሐፍ ግን የተሰጣቸው ተራ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደሚገ ኘው ሳይሆን እንደየተጻፉበት ጊዜ ነው።

ለዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ከፍ ያለ እርዳታ ላደረጉልን ለአቶ እውነቱ እል ሉና ለአቶ ግርማ ካሣ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

የእኛ ዓላማ አንባቢው ይህን መጽሐፍ በማንበብ ሳይወሰን ከመጽሐፉ በሚ ያገኘው እርዳታ መጽሐፍ ቅዱስን ለራሱ ጥቅምና ደስታ እንዲያነብና የየዘመኑንም ታላላቅ ሰዎች ያበረከቱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንዲጠቀምባቸው ነው።

«እውነትንም ታውቃላችሁ፤ እውነትም አርነት ያወጣችኋል።»

(ዮሐንስ 8፥32)

## መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈባቸው ጥንታውያን ቋንቋዎች

አብዛኛዎቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፉ ሲሆኑ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ግን በግሪክ ቋንቋ የተጻፉ ናቸው። ዛሬ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ከ1000 በሚበልጡ ቋንቋዎች ተተርጉሞአል። በ500 ዓ. ም. ገደማ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ግዕዝ ተተረጐመ። ከዚያም በኋላ ከግዕዝ ወደ አማርኛ በ1835 ዓ. ም. ተተረጐመ።

## የጥንት ጽሑፎች

ብዙ መሬትን እየቈፈሩ የጥንት ነገሮችን የሚያጠኑ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱትን ጥንታውያን ከተሞች በመቈፈር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፉትን ብዙ ጽሑፎችን በማግኘታቸው መጽሐፍ ቅዱስ ጥንታዊ መጽሐፍ መሆኑን ይናገራሉ።

በቅርብ ጊዜ በከነዓን በረሀ በየዋሻዎች ውስጥ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከሚገኙት መጻሕፍት አብዛኛዎቹ ተገኝተዋል። ከነዚህም ዋነኛው የኢሳይያስ መጽሐፍ ነበር። ይህ መጽሐፍ በ200 ዓመተ ዓለም የተጻፈ ሲሆን ፤ በዘመቻ ጊዜ በዋሻ እንደ ሸሸጉት ቀረ። የከነዓን አየር ጠባይ በጣም ደረቅ ስለ ሆነ መጽሐፉ ሳይበሰብስ እስከ ዛሬ ድረስ በደኅና ቆየ።

የድሮ ዘመን የጽሕፈት መሣሪያዎች ከዛሬዎቹ በጣም የተለዩ ነበሩ። በብሉይ ኪዳን ዘመን ሦስት ዋና ዋና ዘዴዎች ነበሩ።

1. በወንዝ ዳር በሚበቅል ፓፓይረስ ከተባለ ተክል እንደ ወረቀት ያለ ነገር ሠርተው ነበር። የግብፅ አየር ደረቅ በመሆኑ ለብዙ ጊዜ ሳይበሰብስ በመቆየቱ እንዲህ ያለው ጽሑፍ እስከ ዛሬ ድረስ እየተገኘ ይነበባል።

2. አብዛኛውን ጊዜ ከበግ ወይም ከፍየል አንጋሬ ብራና እያዘጋጁ ይጽፉ ነበር። ይሁን እንጂ ብራናው ከፓፓይረስ ወደድ ይል ነበር። ደግሞም እርጥበት ሲያገኘው ይበሰብሳል።

3. በአሦር ፣ በባቢሎን ፣ በፋርስም ሆነ በሌላ አገር በጭቃ ላይ መጻፍ የተለመደ ነበር። የሚጻፈውም ሹል በሆነ ሽምበቆ ነበር። የተጻፈበትንም ጭቃ በእሳት እየለበለቡ ያጠነክሩት ስለ ነበረ እንዲህ ያለው ጽሑፍ ከብዙ ሺህ ዓመታት በኋላ ተገኝቶልአ ፤ በዚህም የጥንታውያንን ሰዎች ሁኔታና ኑሮ ለማወቅ ተችሎአል።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጠቅላላ አከፋፈል

መጽሐፍ ቅዱስ በሁለት ክፍሎች ይከፈላል። እነዚሁም ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን ናቸው።

## የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት መቼ እንደ ተጻፉ

ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በመጀመሪያ የተጻፈው መጽሐፈ ኢዮብ ነው። ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በግምት ከ1500 ዓመተ ዓለም በፊት ነው። ቀጥሎ የተጻፉት

ሙሴ የጻፋቸው ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም ያሉት መጻሕፍት ሲሆኑ ፤ የተጻፉትም በ1500 ዓመተ ዓለም ነው ። መጽሐፈ ኢያሱ ከነዚህ መጻሕፍት በኋላ በ1400 ዓመተ ዓለም ተጻፈ ። መጽሐፈ መሳፍንት በ1100 ዓመተ ዓለም ተጻፈ ። ሩት በዚሁ በ1100 ዓመተ ዓለም ገደማ የተጻፈ ይመስላል ። ፩ ና ፪ ሳሙኤል በ1100 ዓመተ ዓለም ፤ መዝሙር ፥ ምሳሌ ፥ መኃልየ መኃልይና መክብብ በ1000 ዓመተ ዓለም ፤ ፩ ና ፪ ነገሥት በ600 ዓመተ ዓለም የተጻፉ ሲሆኑ ፤ ፩ ና ፪ ዜና ፥ ዕዝራ ፥ ነህምያና አስቴር በ500 ዓመተ ዓለም የተጻፉ ናቸው ።

የትንቢት መጻሕፍት ግን በሦስት ተከፍለዋል ። እነዚሁም ከምርኮ በፊት የተጻፉት አሥራ አንዱ መጻሕፍት ፥ በምርኮው ጊዜ የተጻፉት ሁለቱ መጻሕፍት ፥ ማለት ዳንኤልና ሕዝቅኤል ፤ ከምርኮው ባኋላ የተጻፉት ሦስቱ መጻሕፍት ፤ ማለት ሐጌ ፥ ዘካርያስና ሚልክያስ ናቸው ። ሚልክያስ የብሉይ ኪዳን የመጨረሻው መጽሐፍ ነው ። ስለዚህ በብሉይ ኪዳን ኢዮብ የመጀመሪያው ፥ ሚልክያስ የመጨረሻው የትንቢት መጻሕፍት ይባላሉ ።

## የብሉይ ኪዳን ክፍሎች

1. ኦሪት (ዘፍጥረትና የእስራኤል ታሪክ) ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም ።
2. የእስራኤል ታሪክ ፤ ከኢያሱ እስከ አስቴር ።
3. ግጥም ፤ ከኢዮብ እስከ መኃልየ መኃልይና ሰቆቃው ኤርምያስ ድረስ ።
4. ትንቢት ፤ ከኢሳይያስ እስከ ሚልክስያ ፤ ከሰቆቃው ኤርምያስ በቀር ።

## የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ለማን እንደ ተጻፉ

ሀ) ከዘፍጥረት ምዕራፍ ፩ እስከ ፲፩ ድረስ እግዚአብሔር በጠቅላላው ስለ ሰው እንዳሰበ ያሳያል ።

ለ) ከዘፍጥረት ምዕራፍ ፲፪ እስከ ሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ፱ ድረስ አብዛኛው ለአይሁድ እንደ ተጻፈ ልናይ እንችላለን ። የሆኖ ሆኖ እንደ ዮናስ ያሉ አንዳንድ መጻሕፍት ለአሕዛብ ተጽፈዋል ።

## የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዋነኞቹ ክፍሎች

አዲስ ኪዳን በአራት ክፍሎች ይመደባል ። እነዚሁም ፡—

፩. ወንጌል ፤
፪. የሐዋርያት ሥራ ፤
፫. መልእክቶች ፤
፬. ትንቢት ወይም የዮሐንስ ራእይ ናቸው ።

## የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት መቼ እንደ ተጻፉ

ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በመጀመሪያ የተጻፉት ሁለቱ የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቶች ወደ ገላትያና ፩ኛ ተሰሎንቄ ናቸው ። እነርሱም የተጻፉት ምናል

ባት በ47 ዓ. ም. ሳይሆን አይቀርም ። በመጨረሻ የተጻፈው የዮሐንስ ራእይ ሲሆን የተጻፈበትም ጊዜ ምናልባት በ69 ዓ. ም. ይሆናል ።

## ዋነኞቹ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች

ከሌሎቹ ሁሉ ብዙዎቹን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የጻፈው ጳውሎስ ነው ። ቀጥሎም ዮሐንስ ሲሆን ከእርሱ የሚለጥቁት ሉቃስና ጴጥሮስ ናቸው ። የቀሩት ግን አንዳንድ መጻሕፍት ብቻ ነው የጻፉት ።

## በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ቊጥሮችና ምዕራፎች

መጽሐፍ ቅዱስን በመጀመሪያ የጻፉት ሰዎች በምዕራፎችና በቊጥሮች አል ወሰኑትም ። መጽሐፍ ቅዱስ በምዕራፎች የተከፈለው በአሥራ ሦስተኛው መቶ ዓመት በእንግሊዝ አገር ሲሆን ምዕራፎቹ ደግሞ በቊጥር የተከፋፈሉት በ1543 ዓ. ም. በፈረንሳይ አገር ነው ።

## በየገጹ ግርጌ የሚገኙት ጥቅሶች

እነዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ በልዩ ልዩ ስፍራዎች ተመሳሳይነት ያላቸውን ክፍ ሎች የሚያመለክቱ ጥቅሶች በመጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስን በጻፉት ሰዎች የተደረጉ አይደሉም ፤ ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት በምርምር እንደ ትምህርቱ ተመ ሳሳይነት ከልዩ ልዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በማያያዝ በአዲስ ኪዳን ጠቅሰዋቸ ዋል ።

## ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት እንደ ጻፉ

«የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማ ቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል ።»

፪ ጢሞቴዎስ ፫ ፥ ፲፮ና ፲፯ ።

ይህ ጥቅስ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተጻፉ መጻሕፍት ሁሉ በሰው ፈቃድ ሳይ ሆን በራሱ በእግዚአብሔር የተጻፉ መሆናቸውንና ጸሐፊዎቹንም የእግዚአብሔር መን ፈስ ቅዱስ እንዳስጻፋቸው በግልጽ ያረጋግጣል ።

እግዚአብሔር ለእነዚያ ሰዎች አስደናቂና ፍጹም የሆነ ዕውቀት ሰጣቸው ። መጽሐፍ ቅዱስ የጻፉትን ሰዎች የእግዚአብሔር መንፈስ በሦስት ጠቅላላ ሁኔታዎች ረዳቸው ።

1· ከመጻፋቸው በፊት በነበሩት ጊዜያት የሆነውን ሁሉ በግልጽ አሳያ ቸው ። ለምሳሌ ያህል ሙሴ ስለ ኖኅ እውነተኛ ታሪክ ፥ ስለ ምድር ፍጥረትና እንዲ ሁም ስለ ሌሎች ነገሮች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመረዳት ሊጽፍ ቻለ ።

2· መንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስ የጻፉትን ሰዎች የእግዚአብሔርን መልእክት በትክክል በጊዜው ለነበሩት ሕዝቦች እንዲያስተምሩ አደረጋቸው ።

3· መንፈስ ቅዱስ እነዚህን ጸሐፊዎች ወደ ፊት ስለሚሆነው ሁሉ እንዲጽፉና እንዲያስተምሩ ፤ ማለት ትንቢት እንዲጽፉና እንዲናገሩ አደረጋቸው። በሌላ አነጋገር እነዚያ ጸሐፊዎች ያለፈውን ፣ በጊዜው የነበረውንና ወደ ፊት የሚሆነውን በትክክል እንዲናገሩ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ተበረታተው ነበር ማለት ነው ።

# ዘፍጥረት

<u>የተጻፈበት ዘመን</u> ፡— በግምት በ1425 ዓመተ ዓለም ነው ።

<u>ጸሐፊው</u> ፡— ሙሴ ነው ።

<u>ዋና አሳብ</u> ፡— ስለ ትውልድ ፣ ስለ ሰማይና ምድር ፣ ስለ ወንድና ሴት ፣ ስለ ኃጢአት ፣ ስለ ዘርና ቋንቋ ፣ ስለ ሥራ ፣ ስለ መሥዋዕትና ሥልጣኔ ፣ ስለ ሌሎችም ነገሮች አጀማመር መግለጽ ነው ።

<u>አስተዋፅዖ</u> ፡—

1· ፍጥረት (ም· 1—2)
2· የሰው መፈተንና መውደቅ (ም· 3—4)
3· የጥፋት ውኃ (ም· 5—9)
4 የዓለም ሕዝብ ትውልድና ዝርዝር እንዲሁም የቋንቋ መደበላለቅ (ም· 10—11)
5· የአብርሃም ታሪክ (ም· 12—23)
6· የይስሐቅ ታሪክ (ም· 24—26)
7· የያዕቆብ ታሪክ (ም· 27—36)
8· የዮሴፍ ታሪክ (ም· 37—50)

<u>ማስታወሻ</u> ፡—

1 የኖኅ መርከብ ያረፈው በአራራት ተራራ ነበር ። ይህም ስፍራ አሁን በደቡባዊ ሩስያ ይገኛል ።

2· መሬት የሚቈፍሩ መርማሪዎች በምዕራፍ 11 የተሰጠውን (የተገለጠውን) የባቤል ግምብ መሳይ ሕንፃዎች በባቢሎን ብዙ አግኝተዋል ።

3· አብርሃም ይኖርበት የነበረው ከተማ ማለት ኡር ተቈፍሮ በዘመኑ ስለ ነበረው ሁናቴ ሁሉ በብዙ ለማወቅ ተችሎአል። ከቤተ መቅደሱ ፍራሽ ሰዎቹ ለጨረቃ ይሰግዱ እንደ ነበረ ታወቀ ፤ በዚያን ጊዜ በነበረው ትምህርት ቤትም ተማሪዎቹ ምን እንደ ተማሩና እንዳጠኑ የሚገልጹ ብዙ ጡቦች ተገኝተዋል ። ማደሪያ ቤቶቹም ከጡብ የተሠሩ ደንበኛ ፎቅ ቤቶች ነበሩ ። እንዲሁም ብዙ ሌሎች ነገሮች ተገኝተዋል ።

4· የአብርሃም ኪዳን በዘፍጥረት 12 ፣ 1—3 በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ተሰጠ ። ይህ ኪዳን ከአብርሃም ጀምሮ እስከ ክርስቶስ መምጫ ድረስ እግዚአብሔር በአይሁድ መካከል ለሚሠራው ሥራ መሠረት ሆኖአል ። ኪዳኑም ለአብርሃም ብዙ ጊዜ ተደጋገመ። ለልጁ ለይስሐቅና (ዘፍጥ· 26፣3—4) ለልጅ ልጁም ለያዕቆብ ተሰጠ። (ዘፍጥ· 28፣13—15)

5. አብርሃም የአይሁድ ሕዝብ አባት ብቻ ሳይሆን ለአረብ ሕዝቦችም አባት ነው ። የአረብ ወገን አጀማመር እንዴት እንደ ሆነ በምዕራፍ 16 ፤ 19 ፣ 37 ና 38 ፣ 25 ፣ 1—4 ና 23—25 ይገልጻል ።

6. የሰዶምና የገሞራ ከተማዎች አሁን የጨው ባሕር ተብሎ በሚታወቀው ውስጥ እንደ ሆኑ ታስቦአል ።

7. የዮሴፍና የክርስቶስ ታሪክ ይመሳሰላሉ ፤ ምሳሌም ይሆናሉ ።

ሀ) ሁለቱም በወንድሞቻቸው ተጠሉ።
ለ) ሁለቱም ለእንግዶች ተሸጡ (አልፈው ተሰጡ)።
ሐ) ሁለቱም በሩቅ አገር ተዋረዱ ።
መ) በኋላም ከፍ ብለው ተከበ[illegible] ።
ሠ) በወንድሞቻቸውም ላይ ዳኞች ሆኑ ።
ረ) ለወንድሞቻቸውም መዳኛ (መድኃኒት) ሆኑ ።
ሰ) በሕይወታቸውም ምንም በደል አልተገኘም ።

# ዘጸአት

ጸሐፊው ፡— ሙሴ ነው ።

የተጻፈበት ዘመን ፡— በግምት በ1425 ዓመተ ዓለም ነው ።

ዋና ሰው ፡— ሙሴ ነው ።

ዋና አሳብ ፡— የእስራኤል ልጆች ከግብፅ ባርነት ነፃ ስለ መውጣታቸውና ኦሪትን ስለ መቀበላቸው ነው ።

አስተዋፅዖ ፡—

1. የእስራኤል ልጆች በግብፅ እንደ ተጨነቁ (ም. 1)
2. የሙሴ አስተዳደግ (ም. 2)
3. በግብፅ ላይ ከእግዚአብሔር የወረዱት መቅሰፍቶች (ም. 3—12)
4. የእስራኤላውያን ከግብፅ መውጣት (ም. 13—18)
5. ለእስራኤላውያን ሕግ እንደ ተሰጠና ድንኳን እንደ ተሠራ. (ም. 19—40)

ማስታወሻ ፡—

1. ይህ መጽሐፍ ብዙ ምሳሌዎች ይገኙበታል ።

ለምሳሌ ፡— ሀ) የፋሲካው በግ ፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ መታረዱንና ለኃጢአተኞች ደሙን ማፍሰሱን ያመለክታል ።

ለ) እስራኤላውያንን በቀን የደመና ፣ በሌሊት የእሳት ዓምድ ይመራቸው እንደ ነበረ ዛሬም አማኞችን ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ይመራቸዋል ።

ሐ) መና በበረሀ ለእስራኤላውያን እንደ ተሰጠ ክርስቶስ በዚህ ዓለም በእውነት ለሚያምኑት የሕይወት እንጀራ ነው ።

መ) ውኃ ከድንጋይ እንዳገኙ እንዲሁም ክርስቶስ የሕይወት ውኃ ነው ።

ሠ) ሙሴ እጁን ዘርግቶ ለእስራኤላውን እንደ ጸለየ (ም.17 ፥ 8-13) በአሁኑ ዘመን ክርስቶስ እኛ ከዓለም ችግርና መከራ ለማ ረፍና ጠላታችንንም ድል ለማድረግ እንድንችል ያማልድል ናል ። (ዕብ. 7 ፥ 25)

2. ሰንበት ከአይሁድ ሕዝብ በቀር ለሌላ ለማንም አልተሰጠም ። (ዘጸአት 31 ፥ 12—17) ። ዛሬ ግን በዚህ በክርስቲያን ዘመን ከእሑድ በስተቀር ሁሉ የሥራ ቀን ነው ። እሑድን ግን ለእግዚአብሔር በማስረከብ ምስጋና የሚቀርብበት ቀን ነው ።

3. በግብፃውያን ላይ መቅሰፍት ያደረሱባቸው አብዛኛውን ጊዜ ያመለኩ ቸው ነገሮች ነበሩ ። ለምሳሌ ያህል የአባይ ወንዝ ፥ እንቁራሪቶች ፥ ከርማና ሌሎች ንም ልንመለከት እንችላለን ።

## ዘሌዋውያን

የመጽሐፉ ስም ከሌዋውያን ነገዶች የተወረሰ ነው ።

ጸሐፊው ፡— ሙሴ ነው ።

የተጻፈበት ዘመን ፡— በግምት በ1425 ዓመተ ዓለም ሳይሆን አይቀርም ።

የመጽሐፉ መክፈቻ ቃላት ፡— «ቅድስና» ና «ሥርየት» ናቸው ።

ቅድስና በመጽሐፉ ውስጥ እስከ 87 ጊዜ ተጽፎ ይገኛል ።
ሥርየት ደግሞ እስከ 45 ጊዜ ተጽፎ ይገኛል ።

ዋና አሳብ ፡— ስለ እስራኤል ሕዝብ መናገር ነው ።

አስተዋፅዖ ፡—

1. አምስቱ ዓይነት መሥዋዕቶች (ም. 1—7)
2. የክህናት ሕግጋት (ም. 8—10)
3. ለእስራኤል የተሰጡ ልዩ ልዩ ሕጎች (ም. 11—22)
4. የአይሁድ በዓላት (ም. 23)
5. እስራኤላውያን ወደ ተስፋው ምድር ሲገቡ እንዲጠብቁ የተሰጣቸው ትእ ዛዛት (ም. 24—27)

ማስታወሻ ፡—

1. እያንዳንዱ መሥዋዕት የክርስቶስን ሥራ የሚያመለክት ነው ።

2. እነዚህ ሕግጋት የተሰጡት ለአይሁድ ሕዝብና ከእነርሱ ጋር አብረው ይኖሩ ለነበሩት (አይሁድ ላልሆኑት) ሕዝብ ብቻ ነበር እንጂ ለመላው ዓለም አልነበረም ። ይህም ማለት በሙሴ በኩል እግዚአብሔር ይተዳደሩበት ዘንድ የሰጣ ቸው ሕገ—መንግሥት ነበር ። የአይሁድ ሕዝብ ከሌሎች የተለዩ ነበሩ ፤ እግዚ አብሔርም የተመለከታቸው ለብቻቸው ነበር ። ለምሳሌ ግርዘትና ሰንበትን መጠበቅ የአይሁድ ሕዝብ የተለዩ ምልክቶች ነበሩ ። (ዘፍጥ. 17 ፥ 9—14 ፤ ዘጸአ. 31 ፥ 12—17)

3. እንስሳትና ወፎች ንጹሕ የሆኑትና (የሚበሉትና) ንጹሕ ያልሆኑት (የማ ይበሉት) ተለይተው ነበር ። ይህ ሕግ በክርስቶስ ተደመሰሰ ። (ማር. 7 ፥ 19 ፤ እን ዲሁም የሐዋ. 10 ፥ 12—15 ተመልከት ።)

# ዘኍልቍ

ጸሐፊው ፦ ሙሴ ነው ።

የተጻፈበት ዘመን ፦ በግምት በ1425 ዓመተ ዓለም ነው ።

ዋና አሳቡ ፦ እስራኤላውያን ከደብረ ሲና ወደ ከነዓን እስኪ ገቡ ድረስ ለዓርባ ዓመታት የሆነውን ታሪክ መግለጽ ነው ። ከዚህም ዋና አሳብ የምንማረው በእግዚ አብሔር ስናምን በእርሱ ኃይል ፥ አቅድና መሪነት በሕይወታችን ደስታ የሚኖረን መሆኑንና በመጨረሻም የተስፋ ርስታችንን ለመውረስ መቻላችንን ነው ።

አስተዋፅዖ ፦

1. ልዩ ልዩ በመንግሥት የተደራጁ ነገሮች (ም. 1—6)
2. ወደ ፓለስቲና ጉዞ መጀመር (ም. 7—11)
3. የአሮንና የማርያም ማመፅ (ም. 12)
4. ወደ ተስፋ ምድር የተላኩ ሰላዮች (ም. 13—14)
5. በበረሀ መዞር (ም. 15—25)
6. አዲስ ትውልድና ወደ ተስፋ ምድር ለመግባት መዘጋጀት (ም. 26—36)

ማስታወሻ ፦

1. ዝናማ የሆኑት የክርስቶስ ምሳሌዎች ፦
   ሀ) በሙሴ የተመታ ድንጋይ (ም. 20 ፥ 7—11 ፤ 1 ቆሮ. 10 ፥ 4 ተመልከት)
   ለ) የናስ እባብ (ም. 21 ፥ 6—9 ፤ ዮሐ. 3 ፥ 14 ተመልከት)
2. ሰዎች በሰባት ነገሮች እንደ አጕረመረሙ ፦
   ሀ) በመንገድ (11 ፥ 1—3)
   ለ) በምግብ (11 ፥ 4—6)
   ሐ) በኃያላን (ም. 13 ፥ 33)
   መ) በመሪዎች (16 ፥ 3)
   ሠ) በእግዚአብሔር ፍርድ (ም. 16 ፥ 41)
   ረ) በበረሀ (20 ፥ 2—5)
   ሰ) በመና (21 ፥ 5)

3. በምድረ በዳ የእስራኤል ልጆች የደረሱባቸው ከተማዎች ዛሬ ጠፍተዋል ። ከእነርሱም ብዙዎቹ መሬትን እየቈፈሩ በሚያጠኑ ሰዎች ተቈፍረዋል ። እነዚህም አገሮች ዛሬ ደረቅ ፥ በዶና ጥቅመ—ቢስ ናቸው ።

# ዘዳግም

ጸሐፊዎቹ ፦ ሙሴና ምናልባት ኢያሱ ሳይሆኑ አይቀሩም ።

የተጻፈበት ዘመን ፦ በ1408 ዓመተ ዓለም ልክ የእስራኤል ልጆች ወደ ተስፋ ምድር ከመግባታቸው ቀደም ብሎ ነበር ።

ዋና አሳብ ፦ አራቱን የሙሴን መጻሕፍት ትምህርት እንደ ገና መናገር ነው ።

1. የዘፍጥረት መጽሐፍ ፦ እግዚአብሔር አይሁዶችን ከሌሎች ሕዝብ ቅዱሳን እንዲሆኑ መምረጡን ።

2· ዘጸአት ፡— ደኅንነት ማግኘትና በእግዚአብሔር ከባርነት መውጣት ።

3· ዘሌዋውያን ፡— የእግዚአብሔርና የሰዎች ቅድስና ።

4· ዘኁልቁ ፡— የእግዚአብሔር መሪነት ለእግዚአብሔር ሰዎች መገኘት ።

አስተዋፅዖ ፡—

1· በሙሴ መሪነት የሆነ የእስራኤላውያን ታሪክ መደገም ። (ም. 1—4)

2· ከእግዚአብሔር የተሰጡት ሕግጋት ተደጋግመው እንዲነገሩ ፤ ሕዝቡም ሕግጋቱን እንዲከተሉ ምክር መስጠት ። (ም. 5—26)

3· ለሰዎች የተሰጡ ምርጫዎች ፤ በመታዘዝ በረከትን ማግኘት ፤ ባለመታዘዝ ርግማንን መቀበል ። (ም. 27—30)

4· ወደ ፊት የሚሆኑ አንዳንድ ነገሮች መግለጽ ፡—

ሀ) የሙሴ ሞት ።

ለ) ኢያሱ በእግዚአብሔር ኃይል ሥልጣንን ማግኘትና ድል ማድረግ ።

ሐ) የሰዎች በመንፈስ መቀዝቀዝና መቀጣት ። (ም. 31)

5· የመጨረሻዎቹ የሙሴ መዝሙርና በረከት ። (ም. 32—33)

6· በናባ ተራራ ሙሴ የተስፋ ምድርን መመልከትና መሞት ። (ም. 34)

# ኢያሱ ወልደ ነዌ

ጸሐፊው ፡— ምናልባት ራሱ ኢያሱ ሳይሆን አይቀርም ። ምክንያቱም በመጽሐፉ ውስጥ ዋናው ሰው ራሱ በመሆኑ ነው ። ቃዴስ በርኔ በተባለ ስፍራ በእግዚአብሔር ላይ ከዓመፁት እስራኤላውያን የተረፉት ኢያሱና ካሌብ ብቻ ነበሩ ። (ዘኁልቍ 14 ፥ 26—38 ተመልከት ።)

«ኢያሱ» ደኅንነት ማለት ሲሆን «ኢየሱስ» ከሚለው ስም ጋር የተመሳሰለ ነው ።

ታሪኩ የሆነበት ዘመን ፡— ምናልባት ከ1408—1383 ከክርስቶስ ልደት በፊት ይመስላል ።

ዋና አሳብ ፡— ወደ ተስፋ ምድር መመለስና ማሸነፍ ነው ። በዚያን ጊዜ ያዕቆብ ከነ ዓንን ለቅቆ ወደ ግብፅ በሄደ ጊዜ ወደ 400 ዓመታት ተጠግቶ ነበር ።

አስተዋፅዖ ፡—

1· የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግረው ወደ ከነዓን መድረስ ። (ም. 1—5)

2· ከነዓንን ማሸነፍ (ም. 6—12)

3· አገሩ በእስራኤል ነገዶች እንደ ተከፋፈለ ። (ም. 13—22)

4· የመጨረሻው የኢያሱ ምክርና ሞት (ም. 23—24)

ማስታወሻ ፡—

1· ሙሴና ኢያሱ ክርስቶስን ይመስላሉ ። ለምሳሌ ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት ሲያወጣቸው ኢያሱ ደግሞ ወደ ተባረከው ምድር መራቸው ።

2· በአብርሃም ጊዜ እንደ ምልክት የነበረው የግርዘት ደንብ ታደሰ ። (ም. 5)


3· ያልተናዘዝነው ኃጢአት በሕይወታችን መገኘት በአከን ድንኳን እንደ ነበረው ኃጢአት ሁልጊዜ መሸነፍንና ማዘንን ያመጣል ። (ም. 7)

# መሳፍንት

ጸሐፊው ፡—ምናልባት ሳሙኤል ነው ።

ታሪኩ የሆነበት ዘመን ፡—ጸሐፊው ማለት ሳሙኤል በግምት በ1100 ዓመተ ዓለም ሲኖር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘው ታሪክ በግምት ከ1383—1104 (ማለት ለ230 ዓመታት) የተደረገ ነው ።

ዋና አሳብ ፡—የእስራኤል ልጆች ደንበኛ ንጉሥ እንዳልነበራቸውና በእግዚአብሔር ተመርጠው ከጠላቶቻቸው በአዳኑአቸው መሳፍንት መገዛታቸውን መግለጽ ነው ። ይህም አሳዛኝ የሆነ ጊዜ ቀደም ብሎ በሙሴ ተገልጦ ነበር ። (ዘዳግ. 31 ፣ 16—21) ። በሕዝቦቹ ላይ መንፈሳዊና ሥጋዊ መለዋወጥ ሆነ ። ይኸውም ቀጥሎ እንደ ተመለከተው ነው ፡—




አስተዋፅዖ ፡—

1. እስራኤላውያን የከነዓንእ ነዋሪዎች በፍጹም እንዲያጠፉ የተሰጣቸውን ትእዛዝ ሳይፈጽሙ መቅረታቸው ። (ም. 1 ፣ 1—2 ፣ 5)
2. የመጽሐፉ ዋና አርዕስት ፤ ከእግዚአብሔር መራቅ ፣ መጨነቅ ፣ መናዘዝ ፣ የመስፍን መመረጥና መዳን ናቸው ። (ም. 2 ፣ 6—3 ፣ 6)
3. የመጀመሪያው መከራ ፤ የመስጴጦምያ ጠላቶቻቸው ፤ አዳኛቸው ፣ ዳንኤል ። (ም. 3 ፣ 7—11)
4. ሁለተኛው መከራ ፤ የሞዓብያውያን ፣ አሞናውያንና አማሌቃውያን ጠላቶች እንደ ተነሡባቸው ። አዳኛቸው ፣ ናዖድ ። (ም. 3 ፣ 12—31)
5. ሦስተኛ መከራ ፤ ጠላቶቻቸው ፣ ከነዓናውያን ፤ አዳኞቻቸው ፣ ዲቦራና ባርቅ ። (ም. 4—5)

6. አራተኛ መከራ ፤ ጠላቶቻቸው ፣ ምድያማውያን ፤ አዳኛቸው ፣ ጌዴዎን ።
(ም. 6 ፣ 1—8 ፣ 32)

7. አምስተኛ መከራ ፤ ጠላቶቻቸው ፣ አቤሜሌክ ፤ አዳኞቻቸው ፣ ቶላና ኢያ
ዕር ። (ም. 8 ፣ 33—10 ፣ 15)

8. ስድስተኛ መከራ ፤ ጠላቶቻቸው ፣ አሞናውያን ፤ አዳኛቸው ፣ ዮፍታሔ ።
(10 ፣ 6—12 ፣ 15)

9. ሰባተኛ መከራ ፤ ጠላቶቻቸው ፣ ፍልስጤማውያን ፤ አዳኛቸው ፣
ሶምሶን ። (13—16)

10 የሰዎቹ በእግዚአብሔር አለመታመን ምሳሌ ። (ም. 17—18)

11. የሰዎቹ የግብረ ገብነት ምሳሌ ። (ም. 19—20)

## ሩት

ጸሐፊው ፤—ያልታወቀ ነው ፤ ምናልባት ሳሙኤል ይሆናል ።

ታሪኩ የሆነበት ዘመን ፤—በግምት ከ1150—1100 ከክርስቶስ ልደት በፊት በመሳፍ
ንት ዘመን ወደ መጨረሻ ግድም ነበር ።

ዋና አሳብ ፤—አይሁድ ስላገቡች ስለ አንዲት አሕዛባዊት ልጃገረድ መግለጽ ነው ።
እርሷም አማቷን ተከትላ ወደ ከነዓን ሄደች ፤ እዚያም የታላቁ ንጉሥ
ዳዊት አያት ለመሆን በቃች ።

አስተዋፅዖ ፤—

1. የአቤሜሌክ ቤተ ሰብ በሞአብ አገር ። (ም. 1)
2. ሩት ከቦዔዝ ማሳ ውስጥ እንደ ለቀመች ። (ም. 2)
3. ሩት በቦዔዝ አውድማ እንደ ተኛች ። (ም. 3)
4. ሩት የቦዔዝ ሚስት እንደ ሆነች ። (ም. 4)

ማስታወሻ ፤—

1. በዚህች መጽሐፍ ብዙ ምሳሌዎች ይገኛሉ ። ኑኃሚን ፤—በስደት ወደ አምላኩ የሚመለሰውን ክርስቲያን ትመስላለች ። ዖርፋ ፤—የእግዚአብሔርን በረከት የማይቀበለውን ኃጢአተኛ ትመስላለች ። ሩት ፤—የእግዚአብሔርን በረከት የሚቀበ ልና የሚበረክ ኃጢአተኛ ትመስላለች ። ቦዔዝ ፤—የኃጢአተኞች አዳኝ የሆነውን ክርስቶስን ይመስላል ።

2. ሩትና ረዓብ በክርስቶስ የትውልድ መስመር አሕዛብ ነበሩ ። (ኢያሱ 2 ፣ 1 ተመልከት ።)

3. ሞአባውያን ከአብርሃም ወንድም ልጅ ከሎጥ ነገድ ነበሩ ። እነርሱም እውነተኛውን አምላክ አላመለኩም ። ነገር ግን ልጆቻቸውን መሥዋዕት እያቀረቡ ሌላ አምላክ ያመልኩ ነበር ።

## ሳሙኤል ቀዳማዊ

ጸሐፊዎቹ ፤—ሳሙኤል (ምዕራፍ 1—24) ፤ ናትና ጋድ (ም. 25—31) ናቸው ።

ታሪኩ የሆነበት ዘመን ፤—ሳሙኤል በ1068 ዓመተ ዓለም የሞተ ይመስላል ። በዚህ
መጽሐፍ ታሪክ ከ1158—1063 ዓመተ ዓለም የቆየ ይሆናል ።

ዋና አሳብ፦—ሀ) የመሳፍንት ዘመን ማለቅ። (ሳሙኤል የመጨረሻው መስፍን ነበር።)

ለ) የነቢያት መነሣት። (ሳሙኤል የመጀመሪያው ነቢይ ነበር።)

ሐ) የነገሥታት መነሣት። (ሳኦል የመጀመሪያው ንጉሥ ነበር።)

አስተዋፅዖ፦—

1. ዔሊና ሳሙኤል (ም. 1—7)
2. ሳሙኤልና ሳኦል (ም. 8—15)
3. ሳኦልና ዳዊት (ም. 16—31)

ማስታወሻ፦—

1. ዔሊ የኖረው ምናልባት በሶምሶን ጊዜ ነው።

2. ደኅንነት የማኅበራዊ ሳይሆን የግል ጉዳዮችን መሆኑን ከዔሊ ልጆች ልንረዳ እንችላለን። አንድ አባት መልከም የእግዚአብሔር ወዳጅ ቢሆን ልጁ በእርሱ እምነት ሊድን አይችልም። ስለዚህ አባቶችና እናቶች ለልጆቻችሁ ክርስቲያናዊ ትምህርት እንድታስተምሩ ኃላፊነት አለባችሁ ማለት ነው። ለዚሁም የዔሊንና የሐናን ልጆች ምሳሌ በመውሰድ ማመዛዘን እንችላለን።

3. በዚያን ጊዜ ሳሙኤል «በነቢያት ትምህርት ቤት» ውስጥ ትምህርት ጀምሮ ነበር። ይኸ በዚያን ጊዜ በነበረው ሕዝብ ሕይወት ዋና ነገር ነበር። ያ ትምህርት ቤት የዛሬውን መሠረተ ትምህርት ቤት ይመስላል። በትምህርት ቤቱም የንባብ፣ የጽሕፈት እንዲሁም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ይሰጡ ነበር።

4. የሳኦል ታሪክ መጀመሪያውና መጨረሻው አሳዛኝ ነበር። ምክንያቱም እንደ እርሱ ያለ ትሑት ሰው በኩራት ምክንያት በእግዚአብሔር መደገፍን ትቶ በገዛ ኃይሉና ጥበቡ በመደገፉ ነው። እያንዳንዳችን ይህንን ታሪክ ማንበብ ያስፈልገናል።

5. አብዛኛው የዳዊት መዝሙር የተጻፈው ይህ መጽሐፍ በተጻፈበት ጊዜ ነበር። ይህ ታላቅ ሥራ ዳዊት ከፈጸማቸው ነገሮች የበለጠ ሆኖ እስከ ዛሬ ይታሰባል።

## ሳሙኤል ካልዕ

ጸሐፊው፦—አልታወቀም፤እንደ አይሁዶች አፈ—ታሪክ ኤርምያስ ይሆናል።

ታሪኩ የሆነበት ዘመን፦—1063—1023 (40 ዓመታት ያህል) ከክርስቶስ ልደት በፊት ነው።

ዋና አሳብ፦—

የዳዊት አገዛዝ ታሪክ። (ይህ ታሪክ በድጋሚ በ፩ ዜና ምዕራፍ 11—29 ይገኛል።)

አስተዋፅዖ፦—

1. ዳዊት ይሁዳን ብቻ ለሰባት ዓመታት እንደ ገዛ። (ይሁዳ ከ12 ነገዶች አንዱ ነበር።) (ም. 1—4)
2. የዳዊት ድል መንሣት (ም. 5—10)
3. የንጉሡ ችግሮች (ም. 11—19)

ሀ) የንጉሡ ኃጢአትና የደረሰበት ቅጣት ። (ም. 11—12)

ለ) ከዳዊት ልጆች ከአቤሴሎምና ከአምኖን ጠባይ የተነሣ ችግር ። (ም. 13—19)

4. በዳዊት የመጨረሻ ዘመናት የሆኑ ልዩ ልዩ ዓመፆች ፣ ችግሮችና መከራ ዎች ። (ም. 20—24)

ማስታወሻ ፦

1. ምዕራፍ 7 ፥ 16 የዳዊት ኪዳን የተባለው እዚያ የዳዊት ዘሮች በዙፋኑ እንደሚቀመጡና እንደሚነግሡ እግዚአብሔር ስለ ተናገረ ነው ። ይኸውም በውነት ስለ ጌታችን ይናገራል ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእናቱ በማርያምና በእጮኛዋ በዮሴፍ ከዳዊት ዘር ነበር ። ለዚህም ኪዳን የሚሆኑትን ጥቅሶች በዳዊት መዝሙር በም ዕራፍ 89 ቍጥር 3 ፤ 4 ፥ 27—29 ፤ 34—37 ፤ በኢሳይያስ ምዕራፍ 9 ቁጥር 6 ና 7 ፤ በኤ ርምያስ 22 ፥ 29 ፤ 23 ፥ 5—6 ፤ በሉቃስ 1 ፥ 30—33 እንዲሁም ሌሎችን ተመልከት ።

2. ያን ጊዜ የግብፅ መንግሥት ኃይል ደክሞ ነበር ፤ ታላላቅ የሆኑ የአሦ ርና የባቢሎን መንግሥታት ገና አልተነሡም ። የእስራኤል ሕዝቦች ዓለምን አልገ ዙም ፤ ነገር ግን በዚያን ጊዜ ከነበሩት ሕዝቦች በጣም የጠነከሩ ነበሩ ። ቍጥራቸ ውም እስከ አምስት ሚሊዮን ይደርስ ነበር ።

3. በመጨረሻ የዳዊት ኃጢአት በመንግሥቱ ላይ ብዙ ኀዘን አመጣ ። እግ ዚአብሔርም ኃጢአቱን ይቅር አለለት ። ይሁን እንጂ የኃጢአቱና የምኞቱ ፍሬ እስከ ዕለተ ሞቱ ከእርሱ አልተለየም ነበር ።

4. የዳዊት መዝሙር ብዙው ክፍል የተጻፈው በዚያን ጊዜ ነበር ። ይህ ታላቅ ሥራ ዳዊት ከሠራቸው ሥራዎች ሁሉ ምናልባት የበለጠ ሥራ ሆኖ ይቈጠ ራል ።

## ነገሥት ቀዳማዊና ነገሥት ካልዕ

ጸሐፊው ፦ ምናልባት ኤርሚያስ ይሆናል ፤ የሆኖ ሆኖ ግን እውነተኛው ጸሐፊ አይታወቅም ።

ታሪኩ የሆነበት ዘመን ፦ ከ1,023—594 (ለ429 ዓመታት) ዓመተ ዓለም ነው ።

ዋና አሳብ ፦ ከዳዊት ሞት አንሥቶ እስከ እስራኤላውያንና ባቢሎናውያን ምርኮ ድረስ የሆነውን የእስራኤል ታሪክ መግለጽ ነው ። ይኸው ታሪክ በ፪ኛ ዜና ይገኛል ።

አስተዋፅዖ ፦

1. የዳዊት ልጅ የሰሎሞን መንግሥት ፤ ብዙ ሀብት ማግኘትና በኋላም በመ ጨረሻው መውደቅ ። (1. ነገሥት 1—11)
2. የአይሁድ ሕዝብ መከፋፈል ። (1. ነገሥት 12—16)
3. የነቢዩ የኤልያስ ሕይወትና ሥራ ። (2. ነገሥት 17—2. ነገሥት 2)
4. የኤልሳዕ ሕይወትና ሥራ ። (2. ነገሥት 3—13)
5. የእሥራኤላውያን መዋረድና በ122 ዓመተ ዓለም የሰማርያ ከተማ በሦ ርያ መማረክ ። (2. ነገሥት 14—17)

6. የአይሁድ መዋረድ ፤ ዋና ከተማቸው በባቢሎን ንጉሥ በናቡከደነፆር በ594 ዓመተ ዓለም መማረክ። (2. ነገሥት 18–25)

ማስታወሻ ፦

1. እግዚአብሔር በሰጠው ጥበብ መሠረት የሰሎሞን መንግሥት በጣም ዝናማ ነበር። በመጨረሻ ግን አገሩ ከእግዚአብሔር ወደ ሌላ አዘንብሎና የራሱም የሰሎሞን ሕይወት በኀዘን ተሞልቶ ነበር። (ለምሳሌ ያህል መክብብን ተመልከት።) በዚህም ምክንያት አገሩ ለሁለት ሊከፋፈል ቻለ። ይህም የሚያሳየን ምንም እንኳ ጥበብ ቢኖረን ለእግዚአብሔር ባናደርገው ደካማዎችና ወዳቂዎች መሆናችንን ነው።

2. ሀ) የእስራኤል መንግሥት በሳኦል ፣ በዳዊትና በሰሎሞን ጊዜ ተባብሮ ነበር። እያንዳንዳቸው ለአርባ አመታት ገዝተዋል።

ለ) መንግሥቱ ከተከፋፈለ በኋላ ደቡባዊው መንግሥት በባቢሎናውያን እስከ ተማረከ ድረስ ለ389 ዓመታት ሲቆይ ፤ ሰሜናዊው መንግሥት በሶሪያውያን እስከ ተማረከ ድረስ ለ254 ዓመታት ቆይቶአል።

ሐ) ይሁዳ የዳዊት ወገን የሆነ የአንድ ትውልድ መንግሥት ብቻ ነበር። እስራኤላውያን ግን ዘጠኝ ትውልድ መንግሥት ነበራቸው።

መ) ከይሁዳ አሥራ ዘጠኝ ንጉሦችና አንዲት ንግሥት ሲነግሡ አንዳንዶቹ ደጎናዎች ፥ አንዳንዶቹ ደግሞ ክፉዎች ፤ ሌሎቹ ደግሞ ቸልተኞችና ሰነፎች ነበሩ። ከእስራኤል ግን የነገሥታት ቍጥር አሥራ ዘጠኝ ሲሆኑ ሁሉም መጥፎዎች ነበሩ።

ሠ) የይሁዳ ሰዎች ሦስት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር በመመለስ ታድሰው ነበር። ይኸውም በንጉሥ አሳ እና በንጉሥ ኢዮሣፍጥ ጊዜ ነበር። (2. ዜና. 14 ፤ 15 ፤ 17 ፤ 20) ሰሜናዊው መንግሥት ግን ምንም ጊዜ ቢሆን አልታደሰም።

3. መንግሥቱ በተከፋፈለበት ጊዜ ብዙ ነቢያት ነበሩ። እነዚህም ነቢያት ስለ መንግሥቱ ሁናቴ ጽፈዋል። እነርሱም ኤልያስ ፥ ኤልሳዕ ፥ ኢዮኤል ፥ ዮናስ ፥ አሞጽ ፥ ሆሴዕ ፥ ኢሳይያስ ፥ ሚክያስ ፥ ኤርምያስ ፥ ናሆም ፥ ሶፎንያስና ዕንባቆም ነበሩ።

4. ዳንኤልና ወዳጆቹ ኢየሩሳሌም በእርግጥ ከመውደቋ በፊት ተማርከው ወደ ባቢሎን አገር በ614 ዓመተ ዓለም ሄደው ነበር። ሕዝቅኤልና መርዶክዮስም (የአስቴር ዘመድ) ከጥቂት ጊዜ በኋላ በ594 ዓመተ ዓለም ሄደዋል።

# ፩ኛና ፪ኛ ዜና

ጸሐፊው ፦—ምናልባት ዕዝራ ነው።

ዋና አሳብ ፦—የአምላክ ወገን ስለ ሆነው ፤ በተለይ ስለ መሢሑ መምጣት ተስፋ ስለ ነበረው ስለ ይሁዳ መንግሥት ነው። (ይሁዳ ደቡባዊው መንግሥት ነበረ።)

ታሪኩ የሆነበት ዘመን ፦—እንደ 1ኛና 2ኛ ነገሥት ነው። ይኸውም ከ1103 እስከ 594 ዓመተ ዓለም ነው።

አስተዋፅዖ፦

1. የአይሁዶች የጥንት መንግሥት (1ኛ ም. 1—9)
2. የሳኦል መንግሥት መጨረሻ (1ኛ ም. 10)
3. የዳዊት መንግሥት (1ኛ 11—29)
4. የሰሎሞን መንግሥት (2ኛ 1—9)
5. የይሁዳ ንጉሦችና ግዛታቸው ፤ መንግሥቱ ከተከፋፈለ በኋላ (2ኛ 10—36)

ማስታወሻ፦

በመጽሐፈ ነገሥት የሚገኘው ታሪክ አብዛኛው በእነዚህ በዜና መጻሕፍት ውስጥ ይገኛል። ሆኖም መጽሐፈ ዜና ስለ ሃይማኖታዊና ስለ መንፈሳዊ ነገሮች አብዝቶ ያስረዳል። መጽሐፈ ነገሥት ግን ስለ መንግሥቱ አስተዳደር ያስረዳል።

# ዕዝራ

ጸሐፊው፦ካህኑ ዕዝራ ነው። ከዚህም ሌላ መዝሙር 119ኙንና ምናልባትም 1ኛንና 2ኛን ዜና ጽፎአል።

ታሪኩ የሆነበት ዘመን፦ከ544—466 ዓመተ ዓለም (78 ዓመታት ያህል ነበር።)

አስተዋፅዖ፦

1. በ544 ዓመተ ዓለም በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ ፈቃድ የ50,000 አይሁዶች በዘሩባቤል መሪነት ወደ ከነዓን መመለስ። (ም. 1—2)

2. ምንም እንኳ የሰማርያ ሰዎች ቢቃወሙ የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ መሠራቱ። (ም. 3—6)

3. በ466 ዓመተ ዓለም በንጉሡ በአርጤክስስ በተሰጠው ፈቃድ መሠረት በዕዝራ መሪነት 2000 አይሁዶች ወደ ከነዓን መመለስና በመንፈስ መታደስ። (ም. 7—10)

ማስታወሻ፦

1. ከምርኮው በኋላ ከተጻፉት መጻሕፍት መጽሐፈ ዕዝራ የመጀመሪያው ነው። (ሌሎችም ማለት ነህምያ ፥ አስቴር ፥ ሐጌ ፥ ዘካርያስ ፥ ሚልክያ ከዚህ መጽሐፍ እየቀጠሉ እንደ ቅደም ተከተላቸው ተጻፉ።) የሐጌና የዘካርያስ መጻሕፍት ቤተ መቅደስ ሲሠራ ሰዎችን ለማደፋፈር ተጻፉ። (ም. 3—6)

2. ኢየሩሳሌምን በ594 ዓመተ ዓለም ያሸነፈው የባቢሎን መንግሥት በ544 ዓመተ ዓለም በፋርስና በሜዶና መንግሥት እጅ ወደቀ። ቂሮስ የተባለው አዲሱ የፋርስ ገዥ በኢሳይያስ 44፥28—45፥4 ከአንድ መቶ ዓመታት በፊት እንደ ተተነበየው አይሁዶች ወደ ፓለስቲና እንዲመለሱ ፈቀደ። ነገር ግን ብዙዎቹ እዚያው አገር ቆዩ።

3. በምዕራፍ 6 ና 7 መካከል የአስቴር ታሪክ ተጻፈ። ይህም ታሪክ 58 ዓመታት ፈጅቶአል። ከዚህም በተጨማሪ ደግሞ ነቢዩ ዳንኤል የኖረው ፥ የሠራውና መጽሐፉን የጻፈው በዚያን ጊዜ ነው።

# ነህምያ

<u>ጸሐፊው</u>፡—ነህምያ ነው።

<u>ታሪኩ የሆነበት ዘመን</u>፡—453—428 (ለ25 ዓመታት) ከክርስቶስ ልደት በፊት ነው።

<u>ዋና አሳብ</u>፡—የኢየሩሳሌም ግንብ በነህምያ መሠራት። ይኸውም በፋርስ ንጉሥ በአርጤክስስ ፈቃድ ነበር።

<u>አስተዋፅዖ</u>፡—

1. ነህያም ስለ ከተማው ማዘኑ ፤ ለመመለስም ፈቃድ መጠየቁ። (ም. 1—2)
2. የኢየሩሳሌም ግንብ መሠራትና የአይሁድ ጠላቶች መቃወም (ም. 3—7)
3. በዕዝራ መሪነት የተደረገ መንፈሳዊ መታደስና የሕዝቦች መለዋወጥ። (ም. 8—13)

<u>ማስታወሻ</u>፡—

1. ነህምያ ከዕዝራ በኋላ በባቢሎን አሥራ አምስት ዓመታት ቆይቶ ተመለሰ። ዕዝራ በዚያን ጊዜ ቄስ ነበር።

2. የዕዝራ ሥራ መንፈሳዊ ሲሆን የነህምያ ሥራ ግን ስለ አስተዳደር ነበር። ሆኖም ነህምያ በጣም መንፈሳዊ ሰው ነበር። እንደዚሁም በዚህ ዓለም የሚኖር ሰው ሁሉ ሰባኪም ሆነ ማንም በማንኛውም ነገር በራሱ ሳይሆን በእግዚአብሔር ኃይል እየተመካ ሁሉን ሥራ በመንፈሳዊነት መሥራት ተገቢ ነው።

3. በምዕራፍ 2፥5—8 በንጉሥ አርጤክስስ ስለ ኢየሩሳሌም መታደስ የተሰጠው ትእዛዝ በዳንኤል መጽሐፍ በምዕራፍ 9፥24—27 ለሚገኘው ትንቢት መክፈቻ ይሆናል። (መጽሐፈ ዳንኤል ማስታወሻ 7 ተመልከት።)

4. ሰንባላጥና ጦቢያ የተባሉት የነህያም ጠላቶች የሰማርያ ገዢዎች ነበሩ። ሰማርያ ከኢየሩሳሌም 50 ኪሎ ሜትር ርቃ ወደ ሰሜን ትገኛለች። እነዚያ ሰማርያውያን ጥንት አይሁድ የነበሩና በኋላም ከአረመኔዎች ጋር በመጋባት የተለዩና ኢየሩሳሌም እንደ ገና እንድትጠነክር ያልፈለጉ ሰዎች ነበሩ። እነርሱ ከአረመኔዎች ጋር በጋብቻ ስለተዋሃዱ ከአይሁድ ጋር በአንድ ላይ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ሊሰግዱ አይችሉም ነበር። የአይሁዶችና የሰማርያ ሰዎች ጠላትነት የተጀመረው በዚህ ጉዳይ በዚያን ጊዜ ነበር። (ዮሐ. ፬ ፥ ፱ ተመልከት።)

# አስቴር

<u>ጸሐፊው</u>፡—አልታወቀም።

<u>ታሪኩ የሆነበት ዘመኩ</u>፡—492—473 (ለ20 ዓመታት) ከክርስቶስ ልደት በፊት ነው።

<u>ዋና አሳብ</u>፡—ከንጉሡ ቤተ መንግሥት አስቴር በተባለች ልጅ አማካይነት እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዴት እንዳዳነ መግለጽ ነው።

<u>አስተዋፅዖ</u>፡—

1. አባትና እናት የሌላት አስቴር የተባለች ልጅ እንዴት የፋርስ ንግሥት ለመባል እንደ በቃች። (ም. 1 ፥ 1—2—1 ፥ 20)

2. በንጉሡ ላይ ያነሡት ዓመፅና የአስቴር ዘመድ የሆነው መርዶክዮስ የሰ ጠው እርዳታ ። (ም. 2 ፥ 21—23)

3. የሐማን ትልቅ ሥራትና አይሁድ እንዲጠፉ በማለት ለንጉሡ ያሳሰበው ሕግ። (ም. 3)

4. አስቴር ዘመዶችዋን ለማዳን ያቀደችው ድርጊት ። (ም. 4—5)

5. የሐማን ውድቀት፤ የአይሁድ ደኅንነትና የመርዶክዮስ ክብር። (ም. 6—10)

<u>ማስታወሻ</u> ፦

1. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህ መጽሐፍ ከነመኃልየ መኃልይ ጋር የእግ ዚአብሔር ስም የማይገኝበት ነው ። ደግሞም ጸሎት አይገኝበትም ።

2. አሐሺዌሮስ በመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ስሙ ሲታወቅ በአ ዲሱ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ አርጤክስስ ተብሎአል። ስለዚህ ይኸኛው አርጤክስስ በመጽሐፈ ዕዝራ የተጠቀሰው አለመሆኑን መገንዘብ ያሻል ። በዓለምም ታሪክ ውስጥ ዘርሴስ በሚባል ስም ይታወቅ ነበር ። እርሱም የግሪክን አውራጃዎች ለማሸነፍ በሞ ከረ ጊዜ ተሸንፎ እንደ ነበር ታሪክ ያወሳልናል ። በምዕራፍ አንድ የተደረገው በዓል የመጀመሪያውን የአውሮፓ ወረራ ለማክበር ነበር ። ከወረራውም በተመለሰ በአራ ተኛው ዓመት አስቴርን አገባ ።

3. የአስቴር ታሪክ የሆነበት ጊዜ በዕዝራ በስድስተኛውና በሰባተኛው ምዕ ራፍ መከከል ነበር ።

4. በዚያን ጊዜ አይሁዶች በኅዳር ወር ስለ ደኅንነታቸው ያደረጉት በዓል እስከ ዛሬ ድረስ በዓለም ክፍል ሁሉ በአይሁዶች ዘንድ የተከበረ ነው ።

# ኢዮብ

<u>ጸሐፊው</u> ፦ አይታወቅም ።

<u>የተጻፈበት ዘመን</u> ፦ አልታወቀም ። ነገር ግን ብዙ ሊቃውንት በአብርሃም ፥ በይስ ሐቅ ወይም በያዕቆብ ጊዜ ሳይሆን አይቀርም ብለው ያስባሉ ።

<u>ዋና አሳብ</u> ፦ የመጀመሪያው ክፍል በእግዚአብሔር ፈቃድ የእግዚአብሔር ሰው የሆ ነው ኢዮብን ሰይጣን እንዴት እዳሰቃየው ነው ። የመጽሐፉ ዋና ክፍል የኢ ዮብ ወዳጆች በኢዮብ ላይ ሥቃይ ያመጣውን ኃጢአት ለማግኘት መሞከራ ቸውን ይናገራል ። ኢዮብ ራሱ ይህንን አሳብ ቢቃወምም በውነቱ የዚህ የሥቃዩ ምክንያት የሆነውን ለመገንዘብ አልቻለም ። ከእነዚህም ሰዎች አን ዳቸውም ሰይጣን የሚያሠቃየው መሆኑን አልተረዱም ።

<u>አስተዋፅዖ</u> ፦

1. የኢዮብ ሁኔታና በእግዚአብሔር ፊት ሰይጣን እንደ ከሰሰው (ም. 1—2)
2. የኢዮብ ዘመዶች ምክር ። (ም. 3—37)
3. ኢዮብ በእግዚአብሔር ዘንድ መዋረዱ ። (ም. 38—41)
4. የኢዮብና የቤተ ሰቡ የመጨረሻ ውጤት ። (ም. 42)

መጽሐፉ የያዘው ዋና ትምህርት ፦

ሀ) በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ሰይጣን ሰውን በጣም አድርጎ እንደሚጠላና በሰውም ላይ ታላቅ ኃይል እንደ አለው ይገልጻል ።

ለ) እግዚአብሔር ክፉዎች ሰዎችን ብቻ ሳይሆን መልካም የሆኑትንም አንዳንድ ጊዜ እንደዚህ ዓይነት ሥቃይ እንዲደርስባቸው ይፈቅዳል ።

ሐ) እንደ ኢዮብ ያሉ ጻድቃን ሰዎች በመልካም ሥራቸውና በትዕግሥታቸው ለመዠራት ይፈልጋሉ ፤ ነገር ግን ንስሐ መግባት አለባቸው ።

መ) ማንኛውም ሰው ሥቃይን በትዕግሥትና በሰላም ቢቀበል በጠባዩና በሕይወቱ መልካም ፍሬ ያገኛል ።

ሠ) ሰይጣን እኛ በእግዚአብሔር የምንተማመነውን በጣም ስለሚጠላ እግዚአብሔር ካልተከላከለልንና ካልጠበቀን በቀር ወዲያው ያጠፋናል ።

## መዝሙረ ዳዊት

ጸሐፊዎች ፦የዳዊት መዝሙር 150 መዝሙሮችን የያዘ ሲሆን ከእነዚሁም 73 ብቻ በዳዊት ፤ 2 በሰሎሞን ፤ 1 በሙሴ ፤ 24 በሌሎች ልዩ ልዩ ጸሐፊዎች ተጽፈዋል ። ይሁን እንጂ የ50 መዝሙሮች ጸሐፊዎች አልታወቁም ።

የተጻፈበት ዘመን ፦ይህ መጽሐፍ የተጻፈበት ጊዜ ተወስኖ የታወቀ አይደለም ። የሆኖ ሆኖ አብዛኛው በ200 ዓመታት ውስጥ ከዳዊት እስከ ሕዝቅያስ የተጻፉ ናቸው ።

አስተዋፅዖ ፦ይህ የመዝሙር መጽሐፍ እንደ ምስጋና መዝሙሩ አጀማመርና አጨራረስ በአምስት ክፍሎች ሊከፈል ይቻላል ። እነርሱም ፦

ሀ) ከመዝሙር ፩ እስከ ፵፩
ለ) ከመዝሙር ፵፪ እስከ ፸፪
ሐ) ከመዝሙር ፸፫ እስከ ፹፱
መ) ከመዝሙር ፺ እስከ ፻፮
ሠ) ከመዝሙር ፻፯ እስከ ፻፶

ይህ የመዝሙር መጽሐፍ ከሌሎች አምስት መጻሕፍት ጋር ሆነው የግጥም መጻሕፍት ይባላሉ ። የእኛ ግጥም በመጨረሻው የድምፅ አንድነት ይኖረዋል ። የዕብራይስጥ ግጥም ግን ከእኛ የተለየ ነው ። ይኸውም የእነርሱ ግጥም በአሳብና በቃላት ቢመዛዘኑም ልክ እንደ አገራችን ግጥም የመጨረሻዎቹ ፊደላት መገናኘት ሲገባቸው የእነርሱ አይገናኝም ።

## ምሳሌ

ጸሐፊዎች ፦ዋና ጸሐፊው ንጉሥ ሰሎሞን ነው ። የሆኖ ሆኖ ሌሎች ብዙ ጸሐፊዎች በዚህ መጽሐፍ ከሚገኙት ጥበቦች ጨምረዋል ። ከእነዚህም ጸሐፊዎች አንዱ ንጉሥ ልሙኤል ነው ። እነዚህ ጸሐፊዎች እርግጠኛ ጸሐፊዎች ወይም ደራሲያን ሳይሆኑ ለጊዜው በዘመኑ ያስደንቁ የነበሩትን ምሳሌዎች በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የጻፉ ናቸው ።

የተጻፈበት ዘመን ፦ ይህ መጽሐፍ የተጻፈበት ጊዜ የተወሰነ አይደለም ። ነገር ግን ሰው ከብዙ ጊዜ ጀምሮ የሚጠቀምባቸው ምሳሌዎች በመጽሐፉ ውስጥ ተጽፈዋል ።

አስተዋፅዖ ፦ ምንም እንኳ ይህ መጽሐፍ እንደ መዝሙረ ዳዊት በቀላሉ ለመከፋፈል ቢያዳግትም ፤ እንደሚከተለው ሊከፋፈል ይቻላል ።

ሀ) ለልጆች የተሰጠ ምክር (ም. 1—7)
ለ) ስለ ጥበብ ታላቅነት (ም. 8 ና 9)
ሐ) በኃጢአት ስለ መደሰልና ውጤቱ (ም. 10—19)
መ) ተግሣፅና ምክር (ም. 20—29)
ሠ) አጉር የተናገራቸው ምሳሌዎች (ም. 30)
ረ) ንጉሥ ልሙኤል የተናገራቸው ምሳሌዎች (ም. 31)

# መክብብ

ጸሐፊው ፦ ሰሎሞን ሳይሆን አይቀርም ።

የተጻፈበት ዘመን ፦ በሰሎሞን ሕይወት መጨረሻ ግድም በ990 ዓመተ ዓለም ይመስላል ።

ዋና አሳብ ፦ ይህ መጽሐፍ የዚህን ዓለም ኑሮ ያላወቀ ሰው ያለውን አሳብና አስተያየት ይናገራል ። ያለ አግባብ ሲፈጸም ባየውና ባወቀው ነገር ሁሉ ያስባል ። በኑሮው ደስታ ፣ ሀብት ፣ ጥበብ ፣ የዓለምን ነገሮች ሁሉ . . . . እንዴት ለማግኘት እንደ ሞከረ ይናገራል ። ሆኖም ማግኛውም ከንቱ ነው ። እርሱም ድህነትና አነስተኛም ደስታ በማግኘት ብቻ ቆይቶ እንደ እንስሳት መሞት ባይኖር ደጎና ነበር እያለ ያስባል ።

በመጨረሻም እግዚአብሔርን መፍራት ከሁሉ እንደሚበልጥና ሕጉንም መፈጸም የሰው ሁለንተናው እንደሆነ ይገልጻል ። (ም. 12፥13)

የመጽሐፉ ጸሐፊ አንድ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር በመንፈስ የተገናኘና የቀረበ እንደ ነበር ይታያል ። ይኸውም በአሳብ እንጂ በሥጋው አልነበረም ። ከዚያም ቀጥሎ ከእግዚአብሔር ከተለየ በኋላ የኑሮው ዓላማ ጠፋበት ።

ከዚህ መጽሐፍ የሚገኘው ትምህርት ፦ በዓለም ላይ ሦስት የኑሮ አቋሞች አሉ ። እንዚሁም ፦

1. በእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ በመመራት እውነተኛ ደስታን የጨበጠ የኑሮ አቋም ።

2. ሥጋዊ ስሜትን ብቻ ለማርካት ጠፊና ረጋፊ የሆነውን ዓለማዊ ደስታን በማሳደድ የተመረኰዘ የኑሮ አቋም ።

3. እውነተኛ ከእግዚአብሔር የሚገኘውን ሰላምና ደስታ ያልጨበጠና እንደዚሁም ዓለማዊ ደስታን ለማግኘት ቢሞክር ያልተሳካለት ፤ እንዲያው በመከከል በመንጠልጠል ላይ የሚገኝ የኑሮ አቋም ናቸው ።

# መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን

ጸሐፊው ፦ሰሎሞን ነው ።

የተጻፈበት ዘመን ፦በግምት በ1,000 ዓመተ ዓለም ነው ።

ዋና አሳብ ፦ይህ መጽሐፍ የእግዚአብሔር ስም አይገኝበትም። ነገር ግን በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኘው ታሪክ በክርስቲያናዊ ምሳሌ ሲወሰድ በጣም ጠቃሚ ነው ። ለምሳሌ ያህል በመጽሐፉ ውስጥ ከሚገኙት ታሪኮች አንዱን እንጠቅሳለን ።

ሰሎሞን ከአገሩ ወደ ሰሜን በተጓዘ ጊዜ አንዲት ልጃገረድ እንዳገኘ ነው። ሲመለስ ከሚስቶቹ እንደ አንዲቱ ሊያደርጋት ወደ ኢየሩሳሌም ይዟት መጣና በጣም እንድትወደው ለማድረግ ሞከረ። ነገር ግን መጀመሪያ ያጫትን ወይም ተስፋ የሰጠችውን የበጎች እረኛ በማሰብ ሰሎሞንን ከልብ አልወደደችውም። በኋላም የድሮ እጮኛዋን ፍቅር እንድታገኝ በማለት እንድታገባው (እረኛውን) ንጉሡ ፈቀደላት ።

ይህም ሁኔታ ለእኛ ምሳሌነት ያለው ነው። ቆንጆይቱ ልጃገረድ በክርስቲያን ፤ እረኛው ደግሞ በክርስቶስ ይመሰላሉ ። ሰሎሞንም በራስ አሳብና በዓለም ጊዜያዊ ደስታና ምኞት ይመሰላል ። ለጊዜው እኛም በዓለም እንድንኖር ተደረግን ፤ ነገር ግን ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ታማኞች መሆን ይገባናል ። ወደ እርሱም በፍጹም መመለስ አለብን ።

# ነቢያት

መቅድም

ኢሳይያስ የመጀመሪያው ነቢይ አይደለም። ብዙዎቹ ድሮም የእግዚአብሔር ሰዎች እየተባሉ ይጠሩ ነበር ። እነዚህም ነቢያት ለምሳሌ ፦ሙሴ ፥ ሄኖክ ፥ ሳሙኤል ፥ ዳዊት ሌሎችም ናቸው ። እነዚህ ሁሉ ወደ ፊት የሚሆነውን አስቀድመው ተናግረዋል ። በብሉይ ኪዳን ትንቢት የሚናገሩ ብዙ መጻሕፍት አሉ ። ከኢሳይያስ እስከ ሚልክያስ ያሉት መጻሕፍት የትንቢት መጻሕፍት ይባላሉ ።

የትንቢት መጻሕፍት እንደ መጻሕፍቱ ትልቅነትና ትንሽነት ከኢሳይያስ እስከ ዳንኤል ፥ ዋነኞቹ ፤ ከሆሴዕ እስከ ሚክያስ ፥ አነስተኞቹ ተብለዋል ። ከዚህም በጣም የተሻለው አከፋፈል ደግሞ እንደ ባቢሎን ምርኮ ይሆናል ።

ሀ) ከምርኮው በፊት 1ኛ. ለይሁዳ ፥ ማለት ለደቡባዊ መንግሥት የተላኩት ፦ ኢዩኤል ፥ ኢሳይያስ ፥ ኤርሚያስ ፥ ሚክያስ ፥ ናሆም ፥ ዕንባቆምና ሶፎንያስ ናቸው ። 2ኛ. ለእስራኤል ፥ ለሰሜናዊው መንግሥት የተላኩት ፦ሆሴዕ ፥ አሞጽና አብድያ ናቸው ። 3ኛ. ለነነዌ የተላከ ዮናስ ነው ።

ለ) በምርኮው ጊዜ ሕዝቅኤልና ዳንኤል ናቸው ።

ሐ) ከምርኮው በኋላ ሐጌ ፥ ዘካርያስና ሚልክያስ ናቸው ።

የነቢያት ሥራ ምንድር ነበር ? ሥራቸው ብዙ ነበር ።

1. ሰዎች የእግዚአብሔርን መንገድ ትተው በኃጢአት በወደቁ ጊዜ ወይም ከእውነተኛው አምላክ ፈቀቅ ባሉ ጊዜ ይላኩ ነበር ። በመጡም ጊዜ ሰዎች የከፋትን መንገድ ትተው ከኃጢአታቸው ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ መንገር ሥራቸው ነበር ። (ለምሳሌ ያህል ዮናስን ተመልከት ።)

2ኛ.—አንዳንድ ጊዜ በቋሰ ምትክ በንጉሡ ወይም በገዢው ፊት እንደራሴ ይሆኑ ነበር ። እግዚአብሔር መልእክት ወደ ንጉሡ መላክ በፈለገ ጊዜ ፤ ወይም እግዚአብሔር ንጉሡን መጠየቅ በፈለገ ጊዜ ነቢያት መልእክተኞቹ ነበሩ ። (ለምሳሌ ፪ ነገሥት 20 ፡ 12—19 ተመልከት ።)

3ኛ. የነቢያት ሥራ ለወደ ፊት የሚሆነውን ማስታወቅ ነው ። ሥራውንና የሥራውንም ዕውቀት ያገኙት ከእግዚአብሔር ነው ። (፪ ጴጥ. ፩ ፡ ፳፩)

ነቢያት ስለ ሦስት አርእስት ተናግረዋል ። እነርሱም ፦

1. በእግዚአብሔር ስለ ተመረጡ ስለ አይሁድ ሕዝቦች ፤
2. እስራኤልን ስለሚነኩ አሕዛቦች ፤
3. ስለ መሢሑ ናቸው ።

በብሉይ ኪዳን የሚገኙት አሥራ አንድ መጻሕፍት በእነዚህ በሦስቱ መንገዶች ተመርተው ተጻፉ ። የሆኖ ሆኖ ብዙዎቹ ነቢያት የጻፉትን ራሳቸው እንኳ አልተረዱትም ፤ ግልጽ አልሆነላቸውም ። ስለዚሁም መንፈስ ቅዱስ በ1 ጴጥ. 1፡10—12 ይናገራል ።

# ትንቢተ ኢዩኤል

ጸሐፊው ፦—ነቢዩ ኢዩኤል እንደ ሆነ በዚሁ መጽሐፍ ም. 1 ፡ 1 ተገልጾአል ።

የተጻፈበት ዘመን ፦—አስቀድሞ ወይም ከሁሉ በኋላ ለመሆኑ በቂ ማስረጃ አናገኝም ። ብዙ ሊቃውንት እንደሚያስቡት ከማናቸውም ከሚልክያስ ሁሉ በኋላ ሲሆን እኛ ግን ከሌሎች የትንቢት መጻሕፍት ቀደም ብሎ ከ843—808 ዓመተ ዓለም የተጻፈ ይመስለናል ። የተጻፈውም ለደቡባዊ ይሁዳ ነገሥታት ለኢዮአስ ፥ ለአሜስያስና ለዖዝያ ለሕዝቡም ጭምር ነበር ። (2 ዜና. ም. 24—26)

ዋና አሳብ ፦—የኢዩኤል ትንቢት እንደ ሌሎቹ በብሉይ ኪዳን እንደ ሚገኙት ትንቢቶች የቅርቡንና የሩቁን ትንቢት በአንድ ጊዜ ያመለክታል ። አሳቡ የረቀቀ በመሆኑ እኛን እንደሚያስቸግረን እንዲሁም ለእነርሱ አስቸጋሪ ነበር ። ዛሬም የተፈጸመውን ለይተን ለማወቅ ገና አስቸጋሪ ሆኖ ይታየናል ።

አስተዋፅዖ ፦—

1. የሚመጣው የባሰ ፍርድ ምሳሌ በመሆን የደረሰው የአንበጣ መሰደድና የዝናም መጥፋት ቅጣት ። (ም. 1)
2. የጌታ ቀን መምጣት ። (ም. 2)
3. የጌታ ቀን ውጤት ። (ም. 3)
   ሀ) በአሕዛብ ላይ ፍርድና ቅጣት ።
   ለ) የእግዚአብሔር ሕዝብ መታደስ ።

ማስታወሻ ፦—

1. በኢዩኤል ከተነገሩት ትንቢቶች አንዳንዶቹ በራሱ ባይገለጹም እንኳ በኋላ በተጻፉት መጻሕፍት ተገልጸው ነበር ። ለምሳሌ በኢዩኤል 2 ፡ 11 ላለው የዮሐንስ ራእይ 19፡11—21 ተመልከት ። እንዲሁም በኢዩልኤ 2 ፡ 30—32 ያለውን በዮሐንስ ራእይ 6 ፡ 9—17 ከተሰጠው ጋር አመዛዝን ።

2. «የእግዚአብሔር ቀን» ከጌታ ዳግመኛ መምጣት እንሥቶ (ማቴ. 24፥ 29 ና 30)፤ በሕዝቦች ላይ የሚደረገው ፍርድ (ማቴ. 25፥31—46)፤ ለአንድ ሺህ ዓመታት የሚኖረው መንግሥት (ራእ. 20፥1—6)፤ የመጨረሻዎቹ ትንሣኤና ፍርድ (ራእ. 20፥11—15)፤ እንዲሁም የአዲስ ምድር መፈጠር (ራእ. 21) እስከ ሚሆንበት ድረስ ያለው ክፍለ ዘመን ነው።

3. ጴጥሮስ በጰንጤቆስጤ ቀን በሐዋርያት ሥራ 2፥16—18 ስላደረገው ሥራ በኢዩኤል 2፥28 ና 29 በኋለኛው ዘመን መንፈሴን አፈሳለሁ እንደ አለ በሐዋርያቱ የቋንቋ ዕውቀትና ልሳናት ማወቅ ያለው ተፈጽሞአል። የሆና ሆኖ ይህ ትንቢት በዚያን ጊዜ በሙሉ አልተፈጸመም።

# ትንቢተ ዮናስ

ጸሐፊው፥ ዮናስ ነው። «ዮናስ» ርግብ ማለት ነው። የእርሱ ወገን ከሰሜናዊው መንግሥት ከዛብሎን ነገድ ነው።

የተጻፈበት ዘመን፥— ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በዳግማዊ የሮብዓም ዘመነ መንግሥት ነው። ዘመኑም ከ831— 790ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር። ዮናስ በነኢዩኤል፥ አሞጽና ሆሴዕ ጊዜ እንደ ኖረ ይታወቃል።

ዋና አሳብ፥— ይህ መጽሐፍ የነቢዩ ታሪክ ነው። ዮናስ ወደ ነነዌ ሄዶ የሚያስተምርበትንና ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር የሚመልስበትን ትእዛዝ ተቀብሎ ሳይፈጽም በእምቢተኛነት ወደ ሌላ አገር ኰበለለ። ነገር ግን በመጨረሻው ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር መለሰ። ምንም እንኳ የእርሱ ስብከት ታላቅ ንስሐ ወደ ማድረግ አድርሶ ሕዝቡንና ከተማውን ከእግዚአብሔር ጋር ቢያስታርቅ ዮናስን አሳዘነው።

አስተዋፅዖ፥—

1. ዮናስ ከእግዚአብሔርና ከነነዌ እንደ ሸሸ። (ም.1)
2. ዮናስ ተጸጽቶ ወደ እግዚአብሔርና ወደ ነነዌ መመለሱ። (ም. 2)
3. ዮናስ በነነዌ ከተማ ከእግዚአብሔር ጋር እንደ ሄደ። (ም. 3)
4. ዮናስ ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልቶ ከነነዌ እንደ ወጣ። (ም. 4)

ማስታወሻ፥—

1. ብዙ ሰዎች ስለ ዮናስና ታላቁ ዓሣ ይጠራጠራሉ። ነገር ግን በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 11 ከቍጥር 19—30 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ታሪኩ እውነት እንደ ነበረ ያረጋግጣል። እውነትም አንዳንድ ዓሣዎች ትልቅ ከመሆናቸው የተነሣ ሰውን ወይም ማናቸውን ትልቅ ነገር ጉርሰው በጕሮሮአቸው የሚያቆዩ አይታጡም። እንዲያውም አንዳንድ መርከበኞች በዚህ በትልቅ ዓሣ ተውጠው ብዙ ጊዜ ከቆዩ በኋላ በልዩ ልዩ ዘዴዎች ድነው በሕይወት ለመኖር በቅተዋል።

2. ዮናስ ሦስት ቀናት ሙሉ በዓሣው ሆድ ውስጥ ተቀምጦ ስለ ወጣው ታሪክና ክርስቶስ በመቃብር ውስጥ ሦስት ቀናት ተቀምጦ በታላቅ ግርማ የተነሣውን ታሪክ በምናመዛዝንበት ጊዜ በውነቱ የተቀራረበ ይመስላል።

3. አይሁዶች ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋት ወይም ከአገራቸው ውጭ ሌሎችን ወደ እነርሱ ሃይማኖት ለመመለስ ያደረጉት ሙከራ ይህ ብቻ መሆኑን እናውቃለን ። የእነዚያ የነነዌ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መመለስና ከተባለው ቅጣት መዳን በእርግጥ ዮናስን ደስ አላሰኘውም ። ይልቅስ ያሳዘነው የነነዌ ሰዎች የእስራኤል ጠላቶች መሆናቸው ነበር ። ይህችም ነነዌ የተባለች የአሶርያ ዋና ከተማ ከጥቂት ጊዜ በላኋ በ279 ዓመተ ዓለም የእስራኤልን ከተማ አጠፋች ።

# ትንቢተ አሞጽ

<u>ጸሐፊው</u> ፡—አሞጽ ፤ እርሱም ከኢየሩሳሌም ጥቂት ወደ ደቡብ አለፍ ብሎ በሚገኘው መንደር የከብት እረኛ ነበር ። ስብከቱም በሰሜነዊው እስራኤል ነበር ። ግን የተወለደው በይሁዳ አገር ነው ።

<u>የተጻፈበት ዘመን</u> ፡—ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በእስራኤል ንጉሥ በዳግማዊ ኢዮርብአም ፤ በይሁዳ ደግሞ በንጉሥ ዖዝያ ጊዜ ነበር ። ዘመኑም 810 ዓመተ ዓለም ነው ።

<u>ዋና አሳብ</u> ፡—አሞጽ የጻፈው በእስራኤልና በጐረቤቶችዋ ላይ ፍርድና ዡነኔ እንደሚመጣ ነው ። በዚያን ጊዜ እስራኤላውያን በሥልጣኔአቸው ይኩሩ ነበር ፤ ነገር ግን አሞጽ የእነርሱን ሥልጣኔ ከምንም ሳይቈጥር ማላገጫ አደረገው ። ከዚያም ወዲህ 18 ዓመታት ቆይቶ በምርኮኝነት ተሰደዱ ፤ ከተማቸውም ጠፋች ።

<u>አስተዋፅዖ</u> ፡—

1. በእስራኤል ዙሪያ በሚኖሩት ሕዝቦች ላይ የኃጢአት ፍርድ እንደሚሆን ይናገራል ። (ም. 1 ፡ 1—2 ፡ 3)
2. ስለ አይሁድ ኃጢአት ይናገራል ። (ም. 2 ፡ 4—5)
3. ስለ እስራኤል ኃጢአትና ፍርድ ። (ም. 2 ፡ 6—9 ፡ 10)
4. በመጨረሻ ስለሚሆነው ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ መሰብሰብና በእነርሱም ላይ ስለሚሆነው በረከት ይናገራል ። (ም. 9 ፡ 11—15)

<u>ማስታወሻ</u> ፡—

ይህ መጽሐፍ ከብዙ ዓመታት በፊት ሰዎች ከእግዚአብሔር እጅ በረከትንና ደኅንነትን እያገኙ በጭራሽ እግዚአብሔርን እንደ ረሱት ያሳየናል ። በተጨማሪም በዛሬው ዘመን ሰዎች እግዚአብሔርን በጭራሽ ስለ መርሳታቸው እንደሚፈርድባቸው በሰፊው ያስረዳናል ።

# ትንቢተ ሆሴዕ

<u>ጸሐፊው</u> ፡—ሆሴዕ ነው ። እርሱም የእስራኤል መንግሥት ነቢይ ነበር ። «ሆሴዕ» ደኅንነት ማለት ነው ። እንደ ኢያሱና ኢየሱስ የተመሳሰለ ስም ነው ።

የተጻፈበት ዘመን ፦—ሆሴዕ እንደሚለው በአራት ልዩ ልዩ ነገሥታት ዘመነ መንግሥት ለሃምሳ ዓመታት ያህል ትንቢት ተናገረ (ም. 1፥1)። ይህም 778—729 ዓመተ ዓለም ማለት እስከ ሰማርያ መውደቅ ድረስ ነበር። ሰማርያ የእስራኤል ዋና ከተማ ነበረች።

ዋና አሳብ ፦—ሆሴዕ የራሱን ሕይወትና ወረተኛ ሚስቱን ምሳሌ እያደረገ ለእስራኤላውያን ኃጢአታቸውን ገለጠባቸው። ይህ ለእስራኤላውያን የተላከውን የእርሱ መልእክት ከመቶ ዓመታት በኋላ ለይሁዳ የተላከውን የኤርምያስን መልእክት ይመስላል። ሁለቱም የትንቢቶቻቸውን ፍጻሜ ለማየት ችለዋል።

አስተዋፅዖ፦—

1. ሆሴዕ ጎሜር የምትባለውን አመንዝራ ሴት ወድዶ እንዳገባና በፍቅሩም እንደ ጸና ፤ እንዲሁም ሚስቱ ታማኝ አለመሆንዋን ያሳስባል። (ም. 1—3)

2. እስራኤል በእግዚአብሔር ላይ መታመንዋን ያለ ምክንያት ብትተውም እግዚአብሔር ግን ፍቅሩን አላቋረጠባትም ፤ ሆኖም ቅጣት እንደሚደርስበት ይናገራል። (ም. 4—13)

3. እስራኤላውያን በመጨረሻ እንደሚሰበሰቡ ያስታውቃል። (ም. 1)

# ትንቢተ ኢሳይያስ

ጸሐፊው ፦—ከይሁዳ ወገን የሆነ ኢሳይያስ ነው። እርሱም ንጉሣዊ ቤተ ሰብነት ያለው ከኢየሩሳሌም ነዋሪ የሆነ ሰው ነበር።

የተጻፈበት ዘመን ፦—ኢሳይያስ ትንቢት የተናገረው ከሆሴዕና ከሚክያስ ጋር በአንድ ጊዜ ከ770—710 ዓመተ ዓለም ባለው ጊዜ ይመስላል። እንዲሁም ኢሳይያስ በሙሴና በክርስቶስ ዘመን መካከል የኖረ ነው። በእርሱ ጊዜ ሰሜናዊው የእስራኤል መንግሥት በእስራኤላውያን እጅ ወደቀ።

አስተዋፅዖ፦—

1. አንዳንድ የተቀላቀሉ ትንቢቶች አሉ። እነዚሁም ለይሁዳ ስለሚሆነው ፍርድና ቅጣት ፤ እንዲሁም ስለሚኖራቸው ክብር ይናገራል። ደግሞም ሌሎች አንዳንድ አገሮች ፍርድ እንደሚመጣባቸው ይናገራል። (ም. 1—35)

2. የንጉሡ የሕዝቅያስ ታሪክ። (ም. 36—39)

3. ስለ መሢሑ ክርስቶስና ስለ ኋለኛው የእስራኤል ክብር። (ም. 40—66)

ማስታወሻ ፦—

1. ትንቢተ ኢሳይያስ ከዳዊት መዝሙር የሚቀጥለው ትልቁ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው።

2. ኢሳይያስ ከነቢያት ሁሉ ዝናው የታወቀ ነው። ትንቢቶቹም በጣም ሰፊና ጥልቅ አስተያየት ያላቸው ናቸው። በመጽሐፈ ኢሳይያስ ስለ መሢሑ የሚናገሩት ጥቅሶች በብሉይ ኪዳን ታላላቅ ሆነው ይቈጠራሉ።

3. አብዛኛው የክርስቶስ ሕይወት በኢሳይያስ ተነግሮአል። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እንመልከት።

ሀ) ስለ ልደቱ 7 ፥ 14 ፤ 9 ፥ 6
ለ) ስለ ቤተ ሰቡ 11 ፥ 1
ሐ) ስለ ባሕሪው 11 ፥ 2
መ) ስለ ጠባዩ 42 ፥ 1—4
ሠ) ስለ ሞቱ 53 በሙሉ ።

4. የፋርስ ንጉሥ የነበረው ቂሮስ ከመወለዱ 200 ዓመታት አስቀድሞ በስሙ ተጠቅሶአል (ኢሳ. 44 ፥ 28)። ይህ ንጉሥ የኢየሩሳሌም ከተማ እንደገና እንድትሠራ የፈቀደ በመሆኑ በኢሳይያስ ትንቢት ተነግሮአል። (ዕዝራ. 1 ፥ 1—4 ተመልከት።)

5. በዘመኑ ስለ ነበረው የአስተዳደር ሁኔታ ያመለክታል። እንዲሁም ከሌሎች ሕዝቦች ጋር ስለ ሚደረገው ትብብርና እነዚህን ስለ መሰሰሉት ልዩ ልዩ ጉዳዮች ይገልጻል። ሕዝቡም ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስና ለአሕዛብ አማልክት ፥ በቅርብ ላሉ ሁሉ እንዳይሰግዱ ለማድረግ በብዙ ሞክሮአል ።

# ትንቢተ ሚክያስ

<u>ጸሐፊው</u> ፥—ሚክያስ ራሱ ሲሆን ለሰሜናዊውና ለደቡባዊው ፤ ማለት ለእስራኤልና ለይሁዳ መንግሥታት የሰበከው እርሱ ብቻ ነበር ።

<u>የተጻፈበት ዘመን</u> ፥—ሚክያስ የነበረው ሆሴዕ በሰሜን ፤ ኢሳይያስ በደቡብ ይሠሩ በነበረ ጊዜ ከ760—710 ዓመተ ዓለም ሳይሆን አይቀርም ።

<u>አስተዋፅዖ</u> ፥—

1. ስለ ሕዝቡና መሪዎቹ ኃጢአት የተተነበየ ፍርድ ። (ም. 1—3)
2. ስለ ንጉሡ መወለድና ስለ የጽድቅ መንግሥት መቋቋም ። (ም. 4—5)
3. የእግዚአብሔር ልመና ፤ ስለ ሕዝቡ ወደ እውነተኛ አምልኮ መመለስ ። (ም. 6—7)

<u>ማስታወሻ</u> ፥—

1. ከምዕራፍ 4—5 ከተጻፉት ትንቢቶች ብዙው ገና አልተፈጸሙም ። ሆኖም በክርስቶስ ዘመነ መንግሥት ይፈጸማሉ ። በዚያን ቀን ኢየሩሳሌም የዓለም ሕዝቦች መሪ ትሆናለች ።

2. በምዕራፍ 5 ፥ 2 ስለ ክርስቶስ ልደት በቤተ ልሔም እንደሚሆን ተነግሮአል ።

3. በሚክያስ 4 ፥ 3 ፤ እንዲሁም በኢዩኤል 3 ፥ 10 የተጠቀሱት ትእዛዛት ተመሳሳይ አይደሉም ። ይህ እግዚአብሔር በሰዎች ላይ በልዩ ልዩ ክፍለ ጊዜያት ለሚፈጽመው ነገር ሁሉ ደኅና ምሳሌ ነው ። መጽሐፍ ቅዱስ ስናጠና እነዚህን እከፋፈሎች ማሰብ ይኖርብናል ። አለዚያ ግን ከስሕተት ላይ በከንቱ እንወድቃለን ። በኢዩኤል የተጠቀሰው ፥ ክርስቶስ ሳይመጣ ትንሽ ቀደም ብሎ ስለሚሆነው ጦርነት ይናገራል ። በሚክያስ የተጠቀሰው ግን ክርስቶስ ከመጣ በኋላ ስለሚሆነው ሰላማዊ መንግሥት መግለጽ ነው ።

# ትንቢተ ናሆም

ጸሐፊው፦ናሆም ነው። ነገር ግን በውነቱ ስለ እርሱ ታሪክ በእርግጥ አይታወቅም።

የተጻፈበት ዘመን፦ከቴብስና ከነነዌ ከተማዎች መውደቅ መካከል ፤ ማለት ከ671—614 ዓመተ ዓለም የሆነ ይመስላል።

ዋና አሳብ፦ይህ መጽሐፍ የአሶራውያን ዋና ከተማ ስለ ሆነችው ስለ ነነዌ መውደቅና መጥፋት የተጻፈ ነው። ይህች ከተማ ከመውደቋ ከ150 ዓመታት በፊት በዮናስ ስብከት ሕዝቦችዋ ወደ እግዚአብሔር ተመልሰው ነበር። የሆኖ ሆኖ እንደ ገና ከእግዚአብሔር ፊቀቅ ስላሉና ስለ ተውት ለከተማይቱና ለሕዝቡ ሁለተኛ ቅጣትና ፍርድ መጣባቸው።

አስተዋፅዖ፦

1. የእግዚአብሔር ትዕግሥትና ፍርድ። (ም. 1)
2. የነነዌ የመውደቋ መግለጫ። (ም. 2)
3. የነነዌ መጥፋትና ምክንያቶቹ። (ም. 3)

ማስታወሻ፦

1. ስለ ቴብስ መግረክ በምዕራፍ 3፥8 ላይ ይናገራል። ይህች ከተማ የላይኛው ምስር ዋና ከተማ ስትሆን ከካይሮ በስተ ደቡብ 560 ኪ.ሎ ሜትር ያህል ርቀት ነበራት።

2. በ614 ዓመተ ዓለም የነነዌ ከተማ በባቢሎንና በሜዶን እጅ ተማረከች። ይህም ሰሜናዊውን መንግሥት የወረረውና ሕዝቡንም የበታተነው ፤ በይሁዳም ላይ ብዙ ችግር ያደረሰው የአይሁዶች ታላቅ ጠላት መጨረሻ ሆነ። ሕዝቅኤልን በኢየሩሳሌም ያስከበበው (ኢሳ. 36—38) የሰናክሬምና የሌሎችም ታላላቅ መንግሥታት ቤተ መንግሥቶች ተቈፍረው ተገኝተው በብዙ የሚቈጠሩ መጻሕፍቶቻቸውና ፊደሎቻቸው አብረው ስለ ተገኙ እነዚህን በመተርጐም ዛሬ ስለ ሁኔታቸውና ስለ አኗኗራቸው ለማወቅ ተችሎአል።

# ትንቢተ ሶፎንያስ

ጸሐፊው፦ራሱ ሶፎንያስ ከይሁዳ ወገን የሆነ ሲሆን የንጉሡ የሕዝቅያስ ትውልድ (ቤተሰብ) ነው። በ2 ነገሥት ከምዕራፍ 22—23 የእርሱ ስብከት ሰዎች ቀድሞ ከሚያደርጉት ክፉ ሥራቸው በመመለስ እንደ ረዳ እናነባለን።

የተጻፈበት ዘመን፦በግምት ዮዝያ በይሁዳ በነገሠ ጊዜ ከ640—620 ዓመተ ዓለም ታሪኩ የሆነ ይመስላል።

ዋና አሳብ፦ይህ መጽሐፍ እንደ ሌሎቹ የትንቢት መጻሕፍት ስለ ኃጢአት ፥ ስለ ፍርድና ስለ ቅጣት ፤ እንዲሁም ስለ መጨረሻው ጊዜ ይናገራል።

አስተዋፅዖ፦

1. የእግዚአብሔር ፍርድና ቅጣት በይሁዳ ላይ መምጣት። (ም. 1—2፥3)

2. በይሁዳ አቅራቢያና በዙሪያዋ ባሉት ሕዝቦች ላይ ቅጣትና ፍርድ መምጣት ። (ም. 2 ፥ 4—3 ፥ 7)

3. ስለ ወደ ፊቱ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ወደ አምላካቸው መመለስና መሰብሰብ ይናገራል ። (3 ፥ 8—20)

ማስታወሻ ፡—

1. በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የጌታ ቀን ሰባት ጊዜ ተጠቅሶአል ። (ለመረጃ ያህል በመጽሐፈ ኢዩኤል ማስታወሻ ሁለት ተመልከት ።)

2. ኢትዮጵያ የሚል ቃል በምዕራፍ 2 ፥ 12 ፤ ደግሞም በምዕራፍ 3 ፥ 10 ላይ ተጠቅሶ እናያለን ። ነገር ግን ያቺ ኢትዮጵያ ምንም እንኳ የዛሬዪቱን ኢትዮጵያ ስም ብትይዝ የዛሬዪቱ አይደለችም ። ይህች ጥንት ኢትዮጵያ ትባል የነበረችው ከግብፅ ደቡባዊውን ክፍል ይዛ የዛሬውን ሱዳን ጨምራ በሮማውያን ኑቢያ ፥ በግብፃውያን ኩሽ ፡ በግሪኮች ኢትዮጵያ ተብላ ትጠራ የነበረችው ክፍለ አገር ነች ። ይህች አገር ከ748—668 ዓመተ ዓለም ለ80 ዓመታት ያህል የግብፅን አገር አሸንፋ ገዝታለች ።

# ትንቢተ ሶፎንያስ

ጸሐፊው ፡—ሶፎንያስ ነው ። ይህ ሰው ከደቡባዊ መንግሥት ከካህናት ወገን የነበረና ከመወለዱም በፊት የእግዚአብሔር ነቢይ እንዲሆን የተመረጠ ነበር ። ይህ ሰው በጣም መልካም ፥ ሰላማዊና ጸጥተኛ ስለ ነበረ መሪ ለመሆን አልፈለገም ። ምንም እንኳ ሥራውንና ስብከቱን ትቶ ቤቱ ሊመለስ ቢፈልግም ልቡ በመንፈስ ተሞልቶ ስለ ነበረ ሥራውን ለመተው አልቻለም ። (ም. 20 ፥ 9)

በይሁዳ ላይ ስለሚፈጸመው ትንቢት ኀዘኑ በጣም ስለ በዛበት ኀዘንተኛ ነቢይ ተብሎ ይጠራ ነበር ። (ም. 9 ፥ 1) ለእግዚአብሔር ቢያገለግልም ሥራው ምንም ውጤት አላስገኘም ። እርሱም የተጠላና የተናቀ ነበር ። መደብደብና መታሰርም ደርሶበታል ። (ም. 35 ፥15—17)

ኢየሩሳሌም በባቢሎን እጅ ወደቀች ። ሶፎንያስም ከዘመዶቹ ጋር ተሰድዶ በሄደበት በምስር አገር በዘመዶቹ በድንጋይ እንደ ተወገረ ይነገራል ።

የሶፎንያስ ሕይወት በኀዘኑ ብዛት ከብዙ ዓመታት በኋላ የተወለደውን የኢየሱስን ሕይወት ይመስላል ። (ኢሳ. 53 ፥ 3)

የተጻፈበት ዘመን ፡—635—592 ዓመተ ዓለም ነው ። ይኸውም ንጉሥ ኢዮስያስ በይሁዳ ከነገሠበት ጊዜ እንሥቶ ኢየሩሳሌም እስከ ወደቀችበትና ባቢሎንም እስከ ተማረከችበት ጊዜ ነው ።

ዋና አሳብ ፡—የሶፎንያስ ትንቢት በብዙ ነገሮች ከሌሎች ነቢያት ትንቢት ጋር ይመሳሰላል ። እነርሱ እንደሚናገሩትም ስለ ኃጢአት ፥ ስለ ፍርድ ፥ እንዲሁም ወደ ፊት ስለሚሆነው የእስራኤላውያን መሰብሰብ ነው ። ሆኖም ትንቢቱ በመጠኑ ለየት ያለ ይመስላል ። የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲቀጡ ስለ ሆነ ከባቢሎን ጦር ሠራዊት ሳይዋጉ እጃቸውን በመስጠት እንዲማረኩ ነገራቸው ። በዚህ ምክንያት ሶፎንያስ አገሩን ለጠላት አሳልፎ ሰጠ በመባል ሲወቀስ ኖረ ።

የኤርምያስ መጽሐፍ በ2ኛ ነገሥት ከምዕራፍ 22 እስከ 25 ፤ በ2ኛ ዜና ከምዕራፍ 34 እስከ 36 ካለው ሰፊ ታሪክ ጋር ይመሳሰላል ።

<u>አስተዋፅዖ</u> ፡- (የመጽሐፉ መልእክቶችና ዋንኞቹ ነገሮች የተደበላለቁ ስለ ሆነ እየለያዩ ለመከፋፈል አስቸጋሪ ነው ።)

1. የኤርምያስ ለነቢይነት መጠራት (ም. 1)
2. ኤርምያስ ስለ ልዩ ልዩ ትንቢቶችና ምልክቶች የተናገረው ኢየሩሳሌም ከመውደቋ በፊት በ594 ዓመተ ዓለም ነው ። (ም. 2 ፡ 39) ከእነዚህም ትንቢቶችና ምልክቶች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ፡—
   ሀ) ይሁዳ ሰባ ዓመታት በምርኮኝነት እንደምትቆይ ይናገራል ።
   ኤር. 21 ፡ 4—10 ፤ 25 ፡ 11—12
   ለ) እስራኤል ተሰብስበ ወደ ቀድሞ ክብሯ እንደምትመለስ ። ኤር. 23፡3—8
   ሐ) በእስራኤል ላይ ስለሚደርሰው ችግር ። ይህም ችግር በኋለኛው ቀን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከመሰብሰባቸው በፊት ይሆናል ። ኤር. 30-31
   መ) ለዳዊት ስለ ሰጠው ኪዳን መፈጸም ። ኤር. 33 ፡ 14—26
3. ኢየሩሳሌም ከወደቀች በኋላ በፓለስቲና በተነሣው ችግር ምክንያት ወደ ምስር መሸሽ ። (ም. 40—44)
4. ለይሁዳ ጎረቤቶችና በተለይም ለባቢሎን የተነገሩ ልዩ ልዩ ትንቢቶች ። (ም. 45—51)
5. ስለ ኢየሩሳሌም መማረክ መግለጽ ። (ም. 52)

# ሰቆቃው ኤርምያስ

<u>ጸሐፊው</u> ፡—ኤርምያስ ነው ።
<u>የተጻፈበት ዘመን</u> ፡—በ594 ዓመተ ዓለም ግድም ነው ።
<u>ዋና አሳብ</u> ፡—የተወደደችው የኢየሩሳሌም ከተማ በባቢሎን ጦር ሠራዊት ስለ ተማረከች ኤርምያስ እንዴ አዘነላት ።

<u>አስተዋፅዖ</u> ፡—

1. የኢየሩሳሌም መጥፋት (ም. 1)
2. ኢየሩሳሌም የወደቀችበት ምክንያት (ም. 2)
3. የኤርምያስ ኀዘን (ም. 3)
4. ስለ ኢየሩሳሌም መውደቅ የሚገልጹ አሳቦች (ም. 4)
5. የእርዳታ ጸሎት (ም. 5)

<u>ማስታወሻ</u> ፡—1. ይህ መጽሐፍ በትንቢት መጻሕፍት መካከል ቢሆንም በእርግጥ ከግጥም መጻሕፍት ጋር ይቈጠራል ።
2. በዕብራይስጥ ቋንቋ በተጻፈው መጽሐፍ ውስጥ (ም. 1—2) ፤ እንዲሁም ምዕራፍ 4 እያንዳንዱ ቍጥር በፊደላት ተራ ተጽፈዋል ። ምዕራፍ 3 ደግሞ ሦስት ሦስቱን ቍጥሮች በፊደል ተራ ይዘአል ። ይኸውም የዕብራይስጥ ፊደላት 22 ሲሆኑ በምዕራፍ 3 ያሉት 66 ቍጥሮች

እንደ ፊተኞቹ ለብቻቸው ሳይሆን በ22 ተከፍለዋል ማለት ነው። ለምሳሌ ከቊጥር 1—3 ያሉት ጥቅሶች በአንድ የፊደል ተራ የተሰፋ ናቸው።

# ትንቢተ ዕንባቆም

ጸሐፊው፤—ዕንባቆም ነው።

የተጻፈበት ዘመን፤—ምናልባት መጽሐፈ ኤርምያስ በተጻፈበት ዘመን፤ ማለት ከኢየሩሳሌም መውደቅ በፊት በ610 ዓመተ ዓለም፤ ኢዮአቂም በነገሠበት ዘመን ይመስላል።

ዋና አሳብ፤—ነቢዩ በእግዚአብሔር የተመረጡትን አይሁዶች እንዴት እግዚአብሔርን በማያውቁ ሰዎች ችግርና ቅጣት ወደቀባቸው በማለት ይደነቃል። የዕንባቆም ትንቢት ከሌሎች ነቢያት ትንቢት ልዩ ነው። ይኸውም እንደ ስብከት አድርጎ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ አልተናገረም። ነገር ግን ከእግዚአብሔር የተገለጠለትን ጥያቄና ትንቢት እንዲሁ ተናገረ።

አስተዋፅዖ፤—1. እግዚአብሔር እንደ ባቢሎን ያለውን ርጉም አገር እንዴት አያጠፋም የሚል ጥያቄ (ም. 1)

2. መልሱ፤ የእግዚአብሔር ፍርድ በመጨረሻ እንደሚሆን (ም. 2)

3. የምስጋና ጸሎት ወደ እግዚአብሔር እንዳቀረበ (ም. 3)

# ትንቢተ ዳንኤል

ጸሐፊው፤—ዳንኤል ራሱ ነው። እርሱም የ20 ዓመት ወጣት በነበረ ጊዜ በ614 ዓመተ ዓለም ከይሁዳ ወደ ባቢሎን ተማርኮ ነበር። የኖረውም በፋርስ ኃይል ዘመን ሲሆን በሞተበት ጊዜ ዕድሜው ወደ 90 የተጠጋ ነበር።

የተጻፈበት ዘመን፤—ከ614—542 ዓመተ ዓለም ነው።

ዋና አሳብ፤—መጽሐፉ የሚገልጸው ስለ ዳንኤል ታሪክና እንዲሁም ወደፊት ስለ ተፈጸሙትና ስለሚፈጸሙት ልዩ ልዩ ትንቢቶች ነው።

አስተዋፅዖ፤—

1. የዳንኤልና የጓደኞቹ መማረክ። (ም. 1)
2. በባቢሎን ዘመነ መንግሥት የተደረጉ ዋና ዋና ነገሮች።
   ሀ) ስለ ንጉሥ ነቡከደነፆር (ም. 2—4)
   ለ) ስለ ንጉሥ ቤልሻድር (ም. 5)
3. በሜዶን ፋርስ ዘመነ መንግሥት ስለ ተደረጉ ዋና ዋና ነገሮች። (ዳንኤል በአናብስት ጉድጓድ ስለ መጣሉ።) (ም. 6)
4. ስለ አንዳንድ አራዊት በምሳሌ ያመለክታል፤ ወይም ስለ እነርሱ ትንቢት ይናገራል። (ም. 7—8)
5. ስለ ሰባ ሱባዔ (ወይም ሳምንት)፤ ስለ መሢሕ መምጣትና ስለ እስራኤል መሰብሰብ የተነበየው። (ም. 9)

ዳንኤል ከተነበየው ማለት ስለ ታላላቅ መንግሥታትና ሕዝቦች አንዳንዱ ሲፈጸም የቀረው ግን ገና ነው።

ማስታወሻ ፡-

1. የዳንኤል ትምህርት አዳጋች አይደለም ። በኑሮአችንም ልንጠቀምበት እንችላለን ። ነገር ግን የእርሱን ትንቢት የተፈጸመውንና ያልተፈጸመውን ለይቶ ማጥናት አስቸጋሪ ነው ።

2. ይህ መጽሐፍ እግዚአብሔር በአቅዱ ፍጹምነት በዚህ ዓለም ያሉትን ነገሮች ሁሉ እንደሚፈጽምና የዓለምንም ታላላቅ ሕዝቦችና መንግሥታት ታሪክ በእርሱ አቅድና ፈቃድ እንደሚሠሩ ይናገራል ።

3. ይህ መጽሐፍ ስለ መላእክት በብዙ ቦታዎች ይገልጸል ። ደግና ክፉ መላእክት (ሰይጣን) በዘወትር ኑሮአችን እንደሚገጥሙን ይናገራል ። ለምሳሌ ያህል ም. 9፡21ና22 ተመልከት ። እንዲሁም ም. 10 ፡ 10—14 ፤ 20—21 ፤ ም. 12 ፡ 1 ተመልከት ። ሦስቱ ሰዎች በእሳት ሲቃጠሉ አራተኛ ሆኖ የታየው የእግዚአብሔር ልጅ ነበር ። (3 ፡ 25)

4. ነቡከደነፆር ፡ ቤልሻድርና ጢሮስ በጥንታዊ ታሪክ በጣም የታወቁ ናቸው ። በምዕራፍ ዘጠኝ ቍጥር አንድ የተጠቀሰው የሜዶን ዳርዮስ እስከ ዛሬም ድረስ በእር ግጥ ማን እንደ ነበረ አልታወቀም ። ምናልባት ይህ ስም በባቢሎን ይነግሡ የነበሩት የነገሥታት መጠሪያ ወይም የቂሮስ ሌላ ተጨማሪ ስም ይሆን ይሆናል ።

5. ቤልሻድር የባቢሎን ከተማ የጦር ሠራዊቱን አላስገባ በማለት ለመከላከል አስቦ ነበር (ም. 5) ። ነገር ግን ቀሳውስቱ የከተማይቱን በር በመክፈት ሠራዊቱን እንዳስገቡ ጢሮስ በጡብ ድንጋይ ላይ ጽፎ ገልጾአል ።

6. ስለ ታለላቆቹ የዓለም መንግሥታት በልዩ ልዩ ሕልሞች ተንብዮላቸዋል ።

ሀ) የታላቁ ምስል በሕልም መታየት ስለ ባቢሎን ፡ ፋርስ ፡ ግሪክ ፡ ሮሜና በኋላም ስለሚነሣው መንግሥት ይናገራል ። (ም. 2)

ለ) ስለ አራዊት ያየው ራእይ ስለ ባቢሎን ፡ ፋርስ ፡ ግሪክ እንዲሁም ስለ አለፈውና ስለ ወደ ፊቱ የሮማውያን መንግሥት በአንድ ላይ ይናገራል ። (ም. 7)

ሐ) ስለ ሁለቱ አውራ በጎች የታየው ራእይ ስለ ሜዶንና ፋርስ ፤ እንዲሁም ስለ ግሪክ ይናገራል ። (ም. 8)

7. ኢየሩሳሌም እንደ ገና እንድትሠራ ትእዛዝ ከተሰጠ በኋላ (ነህምያ ማስ ታወሻ 4 ተመልከት) መሢሑ እንደሚመጣ እግዚአብሔር ይናገራል ። ይኸውም ከ69 ሱባዔዎች በኋላ ነው ። እያንዳንዱ ሱባዔ የሰባት ዓመታት ዘመን ሲሆን በድምሩ ደግሞ የ483 ዓመታት ዘመን ነው ። (በዚያን ጊዜ ሕዝቡ እያንዳንዱ ዓመት 360 ቀናት አለው በማለት ያስቡ ነበር ።) ይህ ትእዛዝ በ453 ዓመተ ዓለም በአርጤክስስ ተሰጠ ። ከዚህም ከተተነበው 483 ዓመታት በኋላ በ30 ዓመተ ምሕረት ጌታችን ተሰቀለ ። ትን ቢቱ እስከ እዚህ ድረስ ተፈጽሞአል ።

ሰባተኛው ሱባዔ (ሰባት ዓመታት) ገና መፈጸም ነበረበት ። ይህ ሱባኤ በዮሐንስ ራእይ ታላቁ የመከራ ጊዜ (ራእ. 7 ፡ 14) ፤ በትንቢተ ኤርምያስ ደግሞ

የያዕቆብ የመከራ ዘመን (ኤር. 30 ፥ 7) ይባላል። ይህ የመከራ ዘመን በልዩ ልዩ በታዎች ቢጠቀስም በተለይ በማቴዎስ 24 ፥ 9--31፤ በራእይ 6፥8 ፤ 9 ፤ 13--16 ተገልጾአል።

8· በምዕራፍ 11፥ 1—35 ያለው ትንቢት በብሉይና አዲስ ኪዳኖች መካከል በነበረው ዘመን ውስጥ ተፈጽሞአል። የእስክንድር ታላቅ መንግሥት በአራት ወገኖች ተከፈለ (ም. 8፥22 ተመልከት)። ከእነዚህም ሁለቱ አሦርያ ከሰሜን ፥ ግብፅ ከደብብ ፥ የእስራኤላውያንን አገር ፓለስቲናን ለየራሣቸው በመፈለግ ተዋጉ። ከሦርያ ነገሥታትም አንዱ አንጾኪዮስ የተባለው በኢየሩሳሌም የነበረውን መቅደስ በውስጡ አሳማ በመሠዋቱ አርክሶታል። ይኸውም ወደ 176 ዓመተ ዓለም ግድም የሆነ ታሪክ ነው። (ም· 11 ፥ 31 ተመልከት)። ከቍጥር 35 ቀጥሎ የተዘረዘሩት በዓለም ታሪክ አልተገለጹም። ሆኖም የቀረው የዚህ መጽሐፍ ክፍል ትንቢት ነው። የእስራኤል ጐረቤቶች በመጨረሻ ቀን የሚሠሩትን ይናገራል።

በቍጥር 36 የተጠቀሰው ንጉሥ የሰሜንም ሆነ የደቡብ ንጉሥ ሳይሆን በመጨረሻው ቀን የሚነሣው የሮማውያን መንግሥት ገዥ ይመስላል። ደግሞም በ7፥ 23--25፤8፥23--25ና9፥26--27 ተጠቅሶአል። እርሱም ከእስራኤላውያን ጋር ለአንድ ሱባኤ (ሰባት ዓመታት) ጽኑ ቃል ኪዳን ያደርጋል። ነገር ግን በሱባኤው ዕኩሌታ (ማለት 3 1/2 ዓመታት ቆይቶ) ኪዳኑን ያፈርሳል። ወደ ፓለስቲናም ተጉዞ የደቡባዊውን ንጉሥ (የግብፅን ንጉሥ) ይወጋል። ከዚያም አይሁዶች የሚያቀርቡትን መሥዕዋት ሁሉ ያስቀርና እግዚአብሔር ቀርቶ እርሱ እንዲመለክ ያደርጋል። (9፥27፤11፥6ና11)።

በእነዚህ በቀሩት ሦስት ዓመታት ተመንፈቅ ሰይጣን በትልቅ ኃይል ሕዝቡን ያስጨንቃል፤ ያታልላል፤ ታይቶ የማይታወቅ ታላቅ ችግር ያመጣል። የዚህ ታሪክ ሌሎች ክፍሎች በራእይ ፥ ኢዩኤል ፥ ሕዝቅኤልና እንዲሁም በአዲስ ኪዳን በልዩ ልዩ በታዎች ይገኛል። ሆኖም ክርስቲያኖች ስለዚህ የችግር ጊዜ በጣም ማሰብ የለብንም። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ይህ የሰባት ዓመታት የችግር ጊዜ ሳይጀመር ክርስቶስን በአየር ለመገናኘት እንደምንነጠቅ ስለሚገልጽ ነው። (1ቆሮ. 15፥ 51-52) (1ተሰ· 4፥13-18) ይኸውም ችግር ከለቀ በኋላ ክርስቶስ አዲስ መንግሥት በዓለም ላይ በመመሥረት ሊነግሥ ይመጣል፤ እኛም ከእርሱ ጋር እንመላለሳለን። (ማቴ· 24፥29-31 ፤ 25፥31)።

# ትንቢተ ሕዝቅኤል

<u>ጸሐፊው</u>፥—ሕዝቅኤል ነው። እርሱም እንደ ኤርምያስ ቄስ ነበር። በ607 ዓመተ ዓለም ወደ ባቢሎን በምርኮኛነት ተወሰደ።

<u>የተጻፈበት ዘመን</u>፥—ሕዝቅኤል በባቢሎን በምርኮኛነት በነበረበት ጊዜ ሃያ ዓመታት ያህል ትንቢት ተናገረ፤ ይኸውም ከ600—580 ዓመተ ዓለም ነበር።

<u>ዋና አሳብ</u>፥—ይህ መጽሐፍ ወደ ፊት በይሁዳ ላይ ስለሚመጣው ፍርድ፤ በሀገሬዎቹ አሕዛቦች ላይ ስለሚደርስው ዡነኔና ወደ ፊትም ለተሰበሰቡት አይሁዶች ስለሚሆነው ክብር ይናገራል።

አስተዋፅዖ ፦1. የሕዝቅኤል መጠራት (ም. 1—3)
2. በይሁዳ ላይ ስለሚመጣው ቅጣት (ም. 4—24)
3. በአይሁድ አቅራቢያ በሚገኙ ሰዎች ላይ የሚመጣው ቅጣት (ም. 25—32)
4. ስለ እስራኤላውያን በመጨረሻው መሰብሰብ (ም. 33—39)
5. በመጨረሻ ስለሚሠራው ቤተ መቅደስ (ም. 40—48)

ማስታወሻ ፦1. ኤርምያስ ፥ ዳንኤልና ሕዝቅኤል ሁሉም በአንድ ጊዜ (ማለት በምርኮው ጊዜ) ተናገሩ። ኤርምያስ በእስራኤል አገር ለቀሩት ሰዎች ተናገረ። የዳንኤል መልእክት ግን በባቢሎን መንግሥት ለሚያገለግሉ ገዢዎች ሲሆን ፤ የሕዝቅኤል ደግሞ በባቢሎን ለተበታተነው ተራ ሕዝብ ነበር።

2. ክርስቶስ ዙፋኑን ከአነሣ በኋላ ስለሚሠራው አዲስ መቅደስ ከተሰጠው መግለጫ ሌላ (ም. 40—48) በምዕራፍ 37 ስለ ደረቅ አጥንት የተሰጠው ትንቢት ይገኛል። ይህ ራእይ ለብዙ ዓመታት የሞቱ ሆነው በዓለም ስለ ተበታተኑት አይሁዶች እንደገና መሰብሰብ ይናገራል። ከ2,000 ዓመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1940 ዓ. ም. የአይሁድ መንግሥት በፓለስቲን ተቋቋመ። ይህም የመጨረሻዎቹ ቀናት መቃረባቸውን በግልጽ ያሳየናል።

3. ምዕራፍ 38 ና 39 ከእስራኤል ሰሜን ስለሚገኙት ሕዝቦች መጥፋት ይነግሩናል። ይኸውም እስራኤልን ለመውረር በአሰቡ ጊዜ ነው። ጐግ የሚባለው ማጉግ የተባለው አገረ ገዢ ነው። ማስክና ተበል የተባሉት ከተሞች (38 ፥ 3) ምናልባት ዛሬ ሞስኮና ቶቦለስ የሚባሉት ሳይሆኑ አይቀሩም በማለት አንዳንድ ሊቃውንት ይናገራሉ። ጎሜርና ቶጎማር (38 ፥ 6) የዛሬዎቹ የጀርመንና የቱርክ አገሮች እንደ ሆኑ ይታሰባል። (ዘፍጥ. 10 ፥ 2—3 ስለ እነዚህ ሰዎች ይናገራል።)

ይህ ትንቢት እንደሚነግረን በመጨረሻዎቹ ቀናት እነዚህ ሕዝቦች በኅብረት ሆነው እስራኤልን ለመውረር ወደ ደቡብ ይዘምታሉ። እንደ ተቃረቡም ራሱ እግዚአብሔር አብዛኛውን የጦር ሠራዊታቸውን ያጠፋል ፤ የቀሩትም ወደ አገራቸው ይሸሻሉ።

# ትንቢተ አብድዩ

ጸሐፊው ፦—አብድዩ ነው። የስሙ ትርጉም የእግዚአብሔር ባርያ ማለት ነው።

የተጻፈበት ዘመን ፦—በ594 ዓመተ ዓለም በኢየሩሳሌም መውደቅ ጊዜ ነው።

ዋና አሳብ ፦—የኤዶም ነገድ ከያዕቆብ ወንድም ከዔሣው ሲያያዝ የመጣ ሕዝብ ነው። እነርሱም ኢየሩሳሌም በጠላት ስትወድቅና እስራኤላውያንም ሲማረኩ ሁል ጊዜ በጣም ይደሰቱ ነበር (ዘኁልቁ 20 ፥ 14 ተመልከት።) አብድዩም እነዚህ ሕዝቦች በእስራኤል መውደቅ መደሰት እንደማይገባቸው ይናገራል። እግዚአብሔር የመረጣቸውን እስራኤላውያንን ቢቀጣቸውም እንኳ እንደገና እርሱ ራሱ ታላቅ ሕዝብ እንደሚያደርጋቸው ይናገራል።

አስተዋፅዖ ፦ 1. የኤዶም መጥፋት (ቍ. 1—16)
2. የእስራኤል እንደገና መዳን። (ቍ. 17—21)

ማስታወሻ ፦ 1. የአብድዩ መጽሐፍ ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ አጭር ነው ።

2. ሳኦል ፣ ዳዊትና ሰሎሞን ከኤዶም ጋር እየተዋጉ ኤዶም ከእስራኤል አንድ ግዛት ሆና ለብዙ ዓመታት እንድትቆይ አደረጉ ። ከዚህም በኋላ በ300 ዓመተ ዓለም ገደማ ዝናማይቱ በደንጊያ የተከተመችው የፒትራ ከተማ በአረብ ነገዶች እጅ ወደቀች ።

3. በክርስቶስ ዘመን ይሁዳን ይገዙ የነበሩት የሄሮድስ ቤተ ዘመዶች ከኤዶም ነገድ የመጣ ነበር ። ይኸውም በማቴዎስ 2፥1 ፤ 6፥14 በሌሎችም ተገልጸአል ።

# ትንቢተ ሐጌ

ጸሐፊው ፦—ነቢዩ ሐጌ ነው ። እርሱም የተወለደው በምርኮው ጊዜ ሲሆን በዕዝራ 5፥1 እንዲሁም 6፥14 ተጠቅሶአል ።

የተጻፈበት ጊዜ ፦—520 ዓመተ ዓለም ይመስላል ።

ዋና አሳብ ፦—የሐጌ መልእክት የእስራኤል ልጆች ሊሠሩ የጀመሩትን የቤተ መቅደስን ሥራ እንዲፈጽሙ ማደፋፈር ነበር ።

አስተዋፅዖ ፦—1. ሰዎች ቤታቸውን ከእግዚአብሔር ቤት አስቀድመው ስለ ሠሩ ተገሠጹ ። (ም. 1)

2. ሕዝቡ በእግዚአብሔር እንዲታመኑ ተደፋፈሩ ። (ም. 2፥ 1—9)

3. ያለፉት ፍርዶች የሚመጣውም በረከት ከእግዚአብሔር እንደሚሆን ገለጠላቸው ። (ም. 2፥10—23)

# ትንቢተ ዘካርያስ

ጸሐፊው ፦—ዘካርያስ ነው ። ከሐጌ ጋር በአንድነት የኖረ ሲሆን በዘሩባቤል መሪነት ከባቢሎን የተመለሰ ይመስላል ። ይህም ዘካርያስ በመቅደስ ተገድሎአል በማለት ኢየሱስ በንግግሩ የጠቀሰው ሰው ሳይሆን አይቀርም ።

የተጻፈበተ ዘመን ፦—ወደ 530 ዓመተ ዓለም ግድም ይሆናል ።

ዋና አሳብ ፦-የዘካርያስ መልእክቶች ስለ ወደ ፊቱ ኢየሩሳሌም ፤ ስለ እስራኤል ሕዝብና ስለ መሢሑ መምጣት ይናገራሉ ።

አስተዋፅዖ ፦—1. ስለ አለፈው የኢየሩሳሌም መጥፋትና በኋላም ስለምታገኘው ደስታና ክብር አሥር ራእዮች ይገልጻሉ ። (ም. 1—6)

2. የበፊቱን ሐሰተኛ አምልኮ ወደ ፊት በእግዚአብሔር ከሚሆነው እውነተኛ ፣ ልባዊ አምልኮ ያመዛዝናል ። (ም. 7—8)

3. ስለ መጀመሪያውና ሁለተኛው የጌታ መምጣት የሚናገሩ ትንቢቶች ። (ም. 9—14)

ማስታወሻ ፦—

1. በዘካርያስ ውስጥ ስለ ክርስቶስ አንደኛ መምጣት የተሰጠው ትንቢት (ም. 9፥9) ፤ እንዲሁም ስለ ሁለተኛ መምጣቱ የተነበየውን (ም. 12፥10 ፤ ራእ. 1፥7 ተመልከት) በዘካርያስ 13፥6—7 ፤ ደግሞ 14፥4 እናገኛለን ።

2. ክርስቶስ የእስራኤልን ጠላቶች በታላቁ ጦርነት እንደሚያጠፋ በጣም ግልጽ አድርጎ ይናገራል። (ዘካ. 12፥19 ፤ 14፥1—3)
3. ክርስቶስ እንደ ጫፍ (ቅርንጫፍ) ነው። (ዘካ. 3፥8 ፤ 6፥12—13 ፤ ኢሳ. 11፥1 ፤ ኤር. 23፥5 ፤ 33፥15 ተመልከት ።)

# ትንቢተ ሚልክያስ

ጸሐፊው ፦—ሚልክያስ ነው። የስሙም ትርጉም መልእክተኛዬ ማለት ነው። ይህ ስም የዚህች መጽሐፍ ጸሐፊ መጠሪያ ስሙ ይሁን ወይም የማዕረግ ስሙ በዕርግጥ አልታወቀም። ከዚህም በቀር የነቢዩን የቀድሞ ሁኔታ የሚገልጽ ነገር የለም።

የተጻፈበት ዘመን ፦—ሚልክያስ የብሉይ ኪዳን የመጨረሻ ጸሐፊ ነው። የጻፈውም በነህምያ ጊዜ ወደ 400 ዓመተ ዓለም ነው።

ዋና አሳብ ፦—ከነህምያ መንፈሳዊ መታደስ በኋላ (ነህምያ 8፥10) የሕዝቡ ልብ እየ ቀዘቀዘና አምልኮአቸው ሆነ ሕይወታቸው እየተበላሸ ሄደ። በሦስት ልዩ ልዩ ሁናቴዎች ኃጢአት አደረጉ።

ሀ) በእግዚአሐር ፊት
ለ) በጎረቤቶቻቸው ፊት
ሐ) በቤተ ሰቦቻቸው ፊት

ሚልክያስ ወደ እውነተኛው ሕይወት ሊመልሳቸው በመሞከር በቅርብ የሚ መጣውን መሢሕ እንዲመለከቱ ለማድረግ ጻፈላቸው።

አስተዋፅዖ ፦—1. እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለው የምሕረት ፍቅር።
2. የእስራኤል ልጆች እግዚአብሔርን ስለ ናቁና የማይገባም መሥዋ ዕት በመሠዊያው ስላቀረቡ ተግሣጽ። (ም. 1፥6—2፥12)
3. ሰዎች ስለ ጋብቻ በመሳሳት በቀላሉ ስለ ሚፋቱ ተግሣጽ። (ም. 2፥13—16)
4. መሢሑ ሕዝቡን ለማንጻት እንደሚመጣ። (ም. 2፥13—3፥5)
5. ሰዎች ለእግዚአብሔር አሥራት ለመስጠት በመሰሰታቸው የደረ ሰባቸው ተግሣጽ። (ም. 3፥6—15)
6. እግዚአብሔርን በእውነተኛ ልቡና የሚያከብሩ በረከት እንደሚሆንላ ቸው። (ም. 3፥16—4፥6)

ማስታወሻ ፦

1. ሚልክያስ ክርስቶስ ሳይወለድ ከእግዚአብሔር በመጨረሻ የተላከ ነቢይ ነው። እስከ ዛሬ ድረስ ብዙ አይሁዶች ክርስቶስንና የክርስቶስን ወንጌል ስላልተቀ በሉ ፤ ሚልክያስ የአይሁዶች መጽሐፍ ቅዱስ መጨረሻ ነው። በኢየሱስ ዘመን የነበሩ አይሁዶች ተስፋ የተደረገላቸውን መሢሕ መቀበል አልፈቀዱም። እስከ ዛሬም ድረስ እግዚአብሔር መሢሕ እንዲልክላቸው ይጠባበቃሉ። ይህ ነቢይ ከተና ገረ 2400 ዓመታት ይሆነዋል።

2· በሚልክያስ 4 ፣ 5 ና 3 ፣ 1 ላይ የተጠቀሰው ኤልያስ በ፩ ነገሥት የተ ጻፈው እርግጠኛው ኤልያስ አይደለም። ነገር ግን ለምሳሌ የተጠቀሰ ነው። መጥ ምቁ ዮሐንስ መልእክተኛ ሆኖ ለጌታ መንገድ አዘጋጀ። (ሉቃ. 1 ፣ 17 ፤ ማቴ. 11 ፣ 14 ፤ 17 ፣ 11)

3. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ለምን ወደደ ? ለዚህ ምክንያት አና ገኝለትም። ዛሬስ እኛን ለምን ይወደናል ? ለዚሁም ምንም መልስ አናገኝም። እግዚአብሔር ሲመርጠን ከራሱ በቀር ምክንያቱን የሚያውቅ የለም። እርሱ ራሱ እንደ ፈቃዱ ከማድረግ በቀር እኛ ተወዳጆችና መልካሞች ልንሆን አንችልም። እኛ ጽድቁን የናቅን የእግዚአብሔር ጠላቶች እንደ ነበርን መርሳት የለብንም። ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለ ሆነ ወደደን። ከታላቅ ፍቅሩም የተነሣ ምንም እንኳ በመበደላችን ሙታን ብንሆን ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን። በክርስቶስ ኢየሱስም ጸጋን አገኘን ፤ ከእርሱም ጋር ከሙታን በመነሣት በሰማያዊ ስፍራ ከእ ርሱ ጋር አስቀመጠን።

«ጸጋው በእምነት አድኖናል ፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእኛ አይደለም ፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም። እኛ ፍጥረቱ ነንና እንመላለስ በት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስ ቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።» ኤፌ. 2 ፣ 4—10

# በብሉይና በአዲስ ኪዳን መካከል ያሉት ዘመናት

በ400 ዓመታት መካከል ማለት ከነህምያና ከሚልክያስ እስከ ክርስቶስ ልደት ድረስ የተደረጉት ነገሮች የሚከተሉት ናቸው። የፋርስ መንግሥት ፣ ፓለስቲናም ጭምር በታላቁ እስክንድር ሥር በ341 ዓመተ ዓለም ወደቁ። ይህ የታላቁ እስክን ድር መንግሥት ለ10 ዓመታት ቆይቶ እርሱ ከሞተ በኋላ በ4 የጦር መሪዎቹ ተከፈለ። ከነዓን አንድ ጊዜ የሦርያ ፣ አንድ ጊዜ ደግሞ የምስር (ግብፅ) ክፍል በመሆን ተገ ዝታለች። የሦርያ ገዥ የነበረው አንጾክዮስ በ178 ዓመተ ዓለም ኢየሩሳሌምን ማረ ከና ቤተ መቅደሱ ውስጥ አሳማ በመሠዋቱ አረከሰው። ከ4 ዓመታት በኋላ አንድ መቃቢስ የተባለ ቄስ ሕዝቡን በባዕድ ገዢዎቻቸው ላይ እንዲነሡ መራ። በዚህም ምክንያት ለ100 ዓመታት ያህል ያለማቋረጥ ውጊያ ተደረገ። በ71 ዓመተ ዓለም የሮሚ ወታደሮች ፖምፔ በተባለው መሪያቸው አማካይነት ኢየሩሳሌምን ያዙ። ኢየ ሱስ በይሁዳ በቤተ ልሔም እስከ ተወለደበት ጊዜ ድረስ ኢየሩሳሌም በሮማውያን እጅ ነበረች። በዚህም በዳንኤል ምዕራፍ 2 ላይ ስለ አራት የዓለም መንግሥታት የተተነበየው ተፈጸመ።

በዚያን ዘመን ብዙዎቹ የጊዜውን ሁኔታ የሚገልጹና በጊዜውም የተደረጉትን የሚያስረዱ መጻሕፍት ቢጻፉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጨመሩም። በተለይም በአይሁድ ሕዝብ ዘንድ በሃይማኖት ረገድ ከፍ ያለ መለዋወጥ ተደርጎአል። ይኸውም እንደሚከተለው ተመድቦአል፦

1· የእስራኤል ሕዝብ ጣዖት ማምለክ እንደማይገባቸው ተረዱ። በባቢሎን ለ70 ዓመታት በምርኮኛነት በነበሩበት ጊዜ ጣዖቶቻቸውን ሁሉ ጣሉ። ይሁን እንጂ

በእንጨትና በድንጋይ ጣዖቶች ምትክ የሙሴን ሕግጋት እንደ ጣዖት ለማምለክ አዘ ነበሉ። ሕግን በየሁኔታው ሁሉ በመጠበቅ ቅድስናንና ደኅንነትን ለማግኘት በከንቱ ደከሙ።

2. የምኩራብ አስፈላጊነት በዚህን ጊዜ እየታወቀ ሄደ። በአዘቦት ቀን የትምህርት መስጫ ፤ በየቅዳሜውም የመጻሕፍት መሰበኪያ ነበር።

3. የአይሁድ ቋንቋ (ዕብራይስጥ) ቀስ በቀስ እየተረሳ ሄደ። የአረሚ ክን ቋንቋ እንደ ራሳቸው ቋንቋ ይነጋገሩበት ጀመር። ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱም ይህንኑ ቋንቋ በአገራቸው ይነጋገሩበት ነበር። ብሉይ ኪዳን ደግሞ ወደ ግሪክ ቋንቋ ተተረጐመ።

4. አይሁድ በብዙ ክፍል ተከፍለው ነበር።

ሀ) <u>ፈሪሳውያን፤</u>—ከውጭ የሆኑ አሳቦችን በመቃወም የሠለጠኑ ነበሩ። ደኅንነት የሚገኘው የሙሴን ሕግ በጠበቅ መሆኑን ፤ ሌላም ነገር እንዲሁ እየጨማመሩ አስተማሩ። እነርሱ በእርግጥ የክርስቶስ ጠላቶች ነበሩ።

ለ) <u>ጸሐፊዎች፤</u>—ከፈሪሳውያን በሥራቸው ሆነ በእምነታቸው የተመሳሰሉ ነበሩ።

ሐ) <u>ሰዱቃውያን፤</u>—የግሪኮችን አሳብ በመቀበል ብሉይ ኪዳንን የከዱ በይሆንም ስለ ሙታን ትንሣኤ አያምኑም ነበር።

## መሢሑ

እግዚአብሔር መሢሑን እንደሚልክ በብሉይ ኪዳን ተስፋ ተሰጥቶአል። መሢሕ ማለት የተቀባ ማለት ነው። በዕብራይስጥ መሢሕ በግሪክ ልክ ክርስቶስ እንደ ማለት ነው። ብሉይ ኪዳን በሁለት ሁኔታዎች ይመስለዋል። አንደኛ፣ እራሱን ለመሥዋዕት እንደ አቀረበ ትሁት አዳኝ ፤ ሁለተኛ፣ ሕዝቡን ነፃ ሊያወጣ እንደ ሚመጣ ኃይል ንጉሥ።

ከሚልክያስ መልእክትና ከኢየሱስም መምጣት በኋላ ሁሉ ይህ የኋለኛው መሢሕ ማለት ኃይሉ ንጉሥ ከእግዚአብሔር እንደሚመጣ ብዙ ሰዎች ተጠባበቁ። ስለዚህ ነበር በትሁቱ ኢየሱስ ምኞታቸውና ተስፋቸው ሁሉ ያልተፈጸመላቸው። የእግዚአብሔር እቅድ ኢየሱስ አስቀድሞ ስለ ዓለም ኃጢአት የጽቅድ መሥዋዕት እንዲያቀርብና በኋላም ወደ ሰላም በክብር ተመልሶ ባላመኑት ላይ እንዲፈርድ ነው። የመሢሑ የመጀመሪያ ሥራ ከ2,000 ዓመታት በፊት ተፈጽሞአል። የመጨረሻዎቹ ቀናት እየተቃረቡ መሄዳቸውን በዕለታዊ ኑሮአችን በምናስተውልበት ጊዜ ግን የኢየሱስ ዳግመኛ መምጣት ደግሞ እየተቃረበ መሄዱን ልንገነዘብ እንችላለን። ዳግመኛ በሚመጣበት ጊዜ እንደ በፊቱ ትሁትና በሰዎች ዘንድ የሚናቀው ሳይሆን በታላቅ ክብር በሰማይ መላእክት ታጅቦ ይመጣል።